# ትምህርት አሥራ አንድ

## የመጀመሪያ ቀን የ1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ መግቢያ

አንዲት ነቢይ፥ «ክርስቶስ የዛሬ ዓመት ይመጣል። ስለሆነም ሁላችሁም በፍጥነት መጋባት ይኖርባችኋል። ሥራ ያላችሁ ደግሞ ሥራችሁን ለቅቃችሁ ባላችሁ ገንዘብ ራሳችሁን ማስደሰት አለባችሁ። እህል መዝራቱ አስፈላጊ አይሆንም። ባጨዳው ጊዜ እዚህ አትኖሩምና» ስትል ተነበየች። ብዙ ሰዎች አስተዋይ ሽማግሌዎች የሰነዘሩትን ማስጠንቀቂያ ችላ ብለው ምክሯን ተቀበሉ። ወጣቶቹ ስለ ነገ ሳያስቡ የትዳር ጓደኞችን መረጡ። ወዲያውም እነዚህ ልጃገረዶች አረገዙ። ሰዎች ሥራቸውን ለቅቀው ያጠራቀሙትን ገንዘብ ሁሉ መጠቀም ጀመሩ። ንብረቶቻቸውን ሁሉ ሸጡ። በዓመቱ መጨረሻ ላይ ሁሉም ነቢይቱ ክርስቶስ ይገለጣል ባለችው ስፍራ ላይ ተሰበሰቡ። የክርስቶስን መገለጥ እየተጠባበቁና እየዘመሩ ለረጅም ጊዜ ጠበቁት። እርሱ ግን ብቅ አላለም። በሁኔታው ተበሳጭተው ነብይቱን ከቤተ ክርስቲያን አባረሯት። ይሁንና ጥፋቱ ቀድሞውንም ተፈጽሞ ነበር።

አንዳንዶች ክርስቶስ ቃሉን አላከበረም በሚል እምነታቸውን ተዉ። ሥራቸውን የለቀቁት ወጣቶች ሕፃናት ልጆቻቸውን ለመንከባከብ ባለመቻላቸው ትዳራቸውን ጥለው ወደ ከተማ ኮበለሉ። ባሎቻቸው የተለዩአቸው ወጣት ሴቶችም የገቢ ምንጭ ለማግኘት ሲሉ ወደ ሴተኛ አዳሪነት ተሠማሩ። ብዙዎቹ ኑሮ ስለተናጋባቸው በድህነት ይማቅቁ ጀመር። በማኅበረሰቡ ውስጥ ይኸው የእብድ «ጴንጤዎች» ጉዳይ መሳለቂያ ሆነ።

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ክርስቶስ መቼ እንደሚመለስ የሚተነብይ መልእክት ሰምተህ ታውቃለህ? ትንቢቱ ተፈጽሟል? ለ) ይህ የሐሰት ትንቢት በክርስቶ ስም ላይ ምን ጉዳት አስከተለ?

በታሪክ ሁሉ እግዚአብሔር ክርስቶስ የሚመለስበትን ጊዜ ገልጦልናል የሚሉ ሐሰተኛ ወንድና ሴት ነቢያት ታይተዋል። የአውሮፓውያን 2000 ዓመተ ምሕረት ሲቃረብ ብዙ ሰዎች ክርስቶስ ይመለሳል በሚል እምነት ሥራቸውን ለቅቀውና ንብረታቸውን ሸጠው ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዘዋል። ምስሉን ቀርጸው ለማስቀረት የፎቶግራፍ ማንሻ ካሜራም የያዙም ነበሩ። ይሄ ምንኛ ታላቅ ሞኝነት ነው! ምንኛ የእግዚአብሔርን ቃል አለማወቅ ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ የሚመለስበትን ቀን ከአብ በስተቀር ማንም እንደማያውቅ ተናግሯል (ማቴ. 24፡36-44 አንብብ)። እንዲህ ዓይነቱ ሐሰተኛ ትንቢት በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል።

የ1ኛና የ2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቶች የተጻፉት አንዳንድ ሰዎች ክርስቶስ በተወሰነ ቀን እንደሚመጣ ወይም ቀደም ብሎ እንደ መጣና አማኞች ሳይነጠቁ እንደ ቀሩ በመግለጽ ስለረበሿቸው ነበር። ጳውሎስ የዚህች ለጋ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሳይነጠቁ እንዳልቀሩ በመግለጽ ያበረታታቸዋል።

2ኛ ጥያቄ፡- ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ስለ 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ አንብብ። ስለ መጽሐፉ፥ ስለ ደራሲው፥ ለማን እንደ ተጻፈ፥ ስለ ከተማይቱና ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ፥ እንዲሁም መልእክቱ ስለሚያተኩርባቸው ነጥቦች የቀረቡትን አሳቦች ጠቅለል አድርገህ ግለጽ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ጥንታውያን ምሁራን የአዲስ ኪዳን አካላት የሆኑትን ደብዳቤዎች በሚያሰባስቡበት ወቅት የጳውሎስን መልእክቶች በሙሉ በአንድ ክፍል ውስጥ አኑረው ነበር። የጳውሎስን አሥራ ሦስት መልእክቶች ያስቀመጡት በጊዜ ቅደም ተከተል አልነበረም። ይልቁንም በጣም ረጅሙን የሮሜ መልእክት መጀመሪያ ላይ ከዚያም 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስን አስከትለዋል። በመቀጠል በጣም ጠቃሚውን የገላትያ መልእክት፥ ከዚያም ከአራቱ የእሥር ቤት መልእክቶቹ ሦስቱን ማለትም ኤፌሶን፥ ፊልጵስዩስና ቆላስይስን አስፍረዋል። ከቆላስይስ በኋላ አራተኛው የእሥር ቤት መልእክት የሆነውን ፊልሞናን ለማስከተል አልፈለጉም። ለዚህም ምክንያቱ የደብዳቤው አጭርነት ነው። የ1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቶች ከገላትያ መልእክት በኋላ ቢጻፉም፥ ከእስር ቤት መልእክቶች በኋላ እንዲሰፍሩ ተደርገዋል። በመጨረሻም ለጢሞቴዎስና ለቲቶ የተጻፉ መልእክቶች ቀርበዋል።

## የ1ኛና የ2ኛ ተሰሎንቄ ደራሲ

3ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ተሰ. 1፡1 እና 2ኛ ተሰ. 1፡1 አንብብ። ሀ) የእነዚህ ሁለት መጻሕፍት ደራሲ ማን ነው። ለ) እነዚህ መግቢያዎች የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? ሐ) በዚህ ክፍልና በገላ. 1፡1 ደራሲው ራሱን የገለጸባቸው መንገዶች የሚለያዩት እንዴት ነው? መ) እነዚህ መልእክቶች የተጻፉት ለማን ነበር? የመልእክቶቹ ተቀባዮች የተገለጹት እንዴት ነው?

የ1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቶች የሚጀምሩት በተመሳሳይ መንገድ ነው። የመጽሐፉ ደራሲ የሆነው ጳውሎስ ራሱንና ሁለት የቅርብ ባልደረቦቹ የሆኑትን አገልጋዮች (ሲላስና ጢሞቴዎስ) ያስተዋውቃል። ሲላስና ጢሞቴዎስ መልእክቱን ጽፈዋል ማለቱ ተገቢ አይሆንም። እነርሱ ከደራሲው ከጳውሎስ ጋር አብረው የሚሠሩ አገልጋዮች ነበሩ።

## መልእክቱ የተጻፈው ለማን ነበር?

4ኛ ጥያቄ፡- የሐዋ. 17፡1-9 አንብብ። ሀ) በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደተመሠረተች ግለጽ። ለ) ከዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ያለውን ካርታ ተመልከት። ተሰሎንቄ የት ትገኛለች? በአሁኑ ዘመን በየት አገር ውስጥ እንደምትገኝ ግለጽ።

የተሰሎንቄ ከተማ ከፊልጵስዩስ በስተደቡብ ምዕራብ 150 ኪሎ ሜትር ርቃ የምትገኝ ስትሆን፥ የሮም አውራጃ የሆነችው የመቄዶንያ ርእስ ከተማ ነበረች። ተሰሎንቄ ከእስያ ተነሥቶ በግሪክ በኩል ወደ ሮም የሚሄድ ታላቅ የንግድ ጎዳና የሚያቋርጣት ወሳኝ ከተማ ነበረች። በተጨማሪም ተሰሎንቄ የባሕር ወደብና በግሪክ፥ ብሎም በመቄዶኒያ ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድባት ከተማ ነበረች። 200,000 ሕዝብ የሚኖርባት ተሰሎንቄ በመቄዶኒያ አውራጃ ውስጥ ምናልባትም በሕዝብ ብዛትና በብልጽግና ተወዳዳሪ ያልነበራት ሳትሆን አትቀርም።

የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በሁለተኛው የጳውሎስ የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞ ወቅት ነበር። በዚህ ጉዞው ጳውሎስ ወንጌልን ወደ መቄዶኒያ እንዲወስድ መንፈስ ቅዱስን እንደመራው ታስታውሳለህ። ጳውሎስ ያገለገለባት የመጀመሪያዋ ታላቅ ከተማ ፊልጵስዩስ ነበረች። ጳውሎስ እዚያ ከታሠረ በኋላ ከሲላስና ጢሞቴዎስ ጋር በመሆን ሁለት ትናንሽ ከተሞችን አቋርጦ በክልሉ ውስጥ ወደምትገኝ ወደ ሌላዋ ትልቅ ከተማ አመራ። እርሷም የተሰሎንቄ ከተማ ነበረች። ጳውሎስ በተሰሎንቄ ውስጥ መጀመሪያ በምኩራብ ውስጥ ለሚገኙ አይሁዶች፥ ከዚያም ሊሰሙት ለፈቀዱት ሰዎች ሁሉ ወንጌልን ሰበኳል። በዚህ ጊዜ ጥቂት አይሁዶችና አሕዛብ በክርስቶስ በማመናቸው የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች። ይሁንና ብዙም ሳይቆይ በእነዚህ ጥቂት አማኞች ላይ ስደት ተነሣ። ከፊልጵስዩስ በተቃራኒ ስደቱ መጀመሪያ የተነሣው ከአሕዛብ ሳይሆን ከአይሁዶች ነበር። እነዚህ አይሁዶች ሀብታም አሕዛብን ጨምሮ ብዙ ሰዎች ወንጌልን በመቀበላቸው በቅንዓት ተነሣሡ። ጳውሎስና ሲላስን ለመያዝ በመሻት የሕዝብ ሁከት እንዲቀሰቀስ አደረጉ። ሕዝቡ ግን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆነውን እያሶንና የአካባቢውን ክርስቲያኖች ብቻ ነበር

የያዙት። እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በገዢዎች ፊት ቀርበው በመንግሥት ላይ ክህደት ፈጽመዋል በሚል ተከሰሱ። ገዢው የቀረበውን የሐሰት ክስ ከመረመረ በኋላ አማኞቹን በነፃ አሰናበተ።

ጳውሎስና ሲላስ በተሰሎንቄ ከተማ ምን ያህል ጊዜ እንደቆዩ አልተገለጸም። ምናልባትም ለአንድ ወር ያህል ቆይተው ይሆናል። የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ጳውሎስና ሲላስ ለተጨማሪ ችግር እንዳይጋለጡ በማሰብ ከከተማይቱ ፈጥነው እንዲወጡ አድርገዋል። ምንም እንኳ ጳውሎስ በተሰሎንቄ ከተማ ብዙ ጊዜ ሊቆይ ባይችልም፥ ወንጌሉን ለመስበክና እነዚህን አዳዲስ አማኞች ለማስተማር ብዙ ተግቶ ሠርቷል። ነገር ግን ከነበረው አጭር ቆይታ የተነሣ የሚፈልገውን ያህል እውነት ሁሉ ሊያስተምራቸው አልቻለም። ከዚህም የተነሣ ወደ በኋላ በአማኞች መካከል ግራ መጋባት ተከሠተ። ይህም በተለይ የአማኞችን ትንሣኤና የክርስቶስን ዳግም ምጽአት የሚመለከት ነበር። ስለሆነም ጳውሎስ እነዚህን አስተምህሮዎች ለማብራራት ሲል የ1ኛና የ2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቶችን ለመጻፍ ተገደደ።

5ኛ ጥያቄ፦ ሀ) በስደት ወይም በመከራ ጊዜ ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ዓላማና ፍቅር የሚጠራጠሩባቸውን መንገዶች አብራራ። ለ) በእነዚህ ጊዜያት አማኞች የእግዚአብሔርን ፍቅር ማስታወሳቸውና ክርስቶስ እውነታቸውን እንደሚጠብቅ መገንዘባቸው አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሐ) ዮሐ. 10፡38 እና ሮሜ 8፡31-38 አንብብ። ለአማኞች የተሰጡት የተስፋ ቃሎች ምን ምንድን ናቸው? ስደትና መከራ በሚደርስብን ጊዜ እነዚህ የተስፋ ቃሎች እንዴት ያበረታቱናል?

ሁለቱም መልእክቶች የተጻፉት ለተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ነው። እነዚህ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ከስደት ጋር የሚታገሉ አዳዲስ አማኞች ነበሩ። ስለሆነም ጳውሎስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ እውነቶች አንዱን በማቅረብ ሊያበረታታቸው ፈለገ። እነዚህ ሰዎች በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት የእግዚአብሔር አብና የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተሰቦች ሆነው ነበር። ቤቶቻቸውን፥ ሥራዎቻቸውን ሊያጡ፥ ወደ ወኅኒ ቤት ሊወረወሩና ለሞት ሊዳረጉ ቢችሉም፥ እግዚአብሔር አልተለያቸውም ነበር። እነርሱ የእግዚአብሔር ውድ ንብረቶች ነበሩ። ክርስቶስ ተስፋ እንደገባው፥ ማንም ከእጁ ሊነጥቃቸው አይችልም (ዮሐ. 10፡28-29)። ጳውሎስ እንደ ገለጸው ደግሞ፥ ማንም ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለያቸው አይችልም (ሮሜ 8፡31-39)። ከሚጋፈጧቸው ችግሮች ባሻገር የተሰሎንቄ አማኞች በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ አስተማማኝ ዋስትና ነበራቸው።

## የ1ኛ ና 2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቶች የትና መቼ ተጻፉ?

ጳውሎስና የአገልግሎት ተባባሪዎቹ ከተሰሎንቄ ተነሥተው በደቡብ አቅጣጫ ወደ ቤሪያ አቀኑ። በቤሪያ ጳውሎስ በአይሁዶችና በአሕዛብ መካከል ፍሬያማ አገልግሎት በማከናወኑ ቤተ ክርስቲያን ልትመሠረት ቻለች። ይሁንና ብዙም ሳይቆይ አይሁዶች ከተሰሎንቄ መጥተው ሁከት ይፈጥሩ ጀመር። በዚህ ጊዜ ጳውሎስ በስተደቡብ ወደ አቴና ሲያመራ ሲላስና ጢሞቴዎስ በቤሪያ ማገልገላቸውን ቀጠሉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጳውሎስ ጢሞቴዎስና ሲላስ ወደ አቴና እንዲመጡ መልእክት ላከባቸው። ከዚያም

ጳውሎስ፥ በተሰሎንቄ የነበሩት ማኅበረ ምእመናን በኃይለኛ ስደት ውስጥ እንዴት እየተመላለሱ እንዳሉ ያስብ ጀመር (1ኛ ተሰ. 3፥1–5)። ስለሆነም ጢሞቴዎስን ወደ ተሰሎንቄ መልሶ ከላከው በኋላ (ምናልባትም ሲላስ ወደ ፊልጵስዩስ ሄዶ ይሆናል)፥ ጳውሎስ ወደ አቴናና ከዚያም ወደ ቆሮንቶስ አመራ። በኋላ ሲላስና ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር በቆሮንቶስ ከተማ ሲገናኙ (1ኛ ተሰ. 3፥6)፥ ጢሞቴዎስ ስለ ተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ማብራሪያ ሰጠ። የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ጳውሎስን ይወዱትና ያከብሩት፥ ክርስቶስንም በታማኝነት ሊከተሉት ይፈልጉ ነበር። ጢሞቴዎስ ግን በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አንዳንድ ችግሮች መኖራቸውን አመለከተ። ከእነዚህም ችግሮች መካከል ወሲባዊ ኃጢአቶችና ቀደም ሲል የሞቱት አማኞች በሕይወት ካሉት አማኞች ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚመለከቱ ውዝግቦች ነበሩ። ጳውሎስ የ1ኛ ተሰሎንቄን መልእክት የጻፈው በ51 ዓ.ም አካባቢ በሁለተኛው የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞው ወቅት ከቆሮንቶስ ከተማ ነበር። ደብዳቤውን ለጢሞቴዎስ ሰጥቶ ወደ ተሰሎንቄ ከመለሰው በኋላ እዚያው በቆሮንቶስ ከተማ ማገልገሉን ቀጠለ።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ አያሌ ወራት ከተቆጠሩ በኋላ፥ ጳውሎስ ከጢሞቴዎስ ይሁን ወይ ከሌላ ግለሰብ በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ዕልባት ያላገኙ ጉዳዮች መኖራቸውን ሰማ። አንዳንዶች ኢየሱስ በቶሎ እንደሚመለስ በማሰብ ሥራቸውን አቆሙ። የሆነ ሰው ደግሞ በጳውሎስ ስም የክርስቶስን መመለስ የሚገልጽ ደብዳቤ ጽፎላቸው ነበር። ይህም ደብዳቤ በመካከላቸው ውዝግብን አስከተለ። ስለሆነም ጳውሎስ ይህን የ2ኛ ተሰሎንቄ መልእክት የጻፈው የተሰሎንቄ አማኞች ስለ መጨረሻው ዘመን የነበሯቸውን አንዳንድ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች ለማረም ነበር። ይሄኛው መልእክት የተጻፈው የመጀመሪያው መልእክት ከተጻፈ በኋላ ከ3–6 ወራት ባሉት ጊዜ ውስጥ ነው። የመጀመሪያው መልእክት የቆሮንቶስ ከተማ ከ51–52 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ እንደተጻፈ ይታወቃል።

## የ1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቶች ዓላማ

<u>የመጀመሪያው ዓላማ</u>፡– ጳውሎስ ከተሰሎንቄ ከተማ ብዙም ሳይቆይ በፍጥነት መውጣት ስለነበረበት አማኞቹን በእግዚአብሔር ቃል ለማስታጠቅ የሚበቃ ጊዜ አላገኘም ነበር። ከዚህም በላይ የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ ስደት ውስጥ ነበረች። በመሆኑም ጳውሎስ እነዚህ ጥቂት አማኞች ለክርስቶስ ታማኞች እንዲሆኑና በዚህ በጥላቻ በተሞላው አካባቢ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው እንዴት ሊኖሩ እንደሚገባቸው ለማስተማር ፈለገ።

<u>ሁለተኛ ዓላማ</u>፡– የተሰሎንቄ አማኞች ስለ መጨረሻው ዘመን ብዙ ያልተገነዘቧቸው ነገሮች ነበሩ። ጳውሎስ እነዚህን ነገሮች ሊያብራራቸው ፈለገ። ጳውሎስ ለተሰሎንቄ የጻፈው መልእክት ስለ መጨረሻው ዘመን ቁልፍ አሳቦችን አካትቷል። ከዚህ የበለጠ ዝርዝር ጉዳዮችን በአዲስ ኪዳን ውስጥ የምናገኘው ከክርስቶስ ትምህርቶችና ከዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ

ውስጥ ብቻ ነው። በተሰሎንቄ መልእክት ውስጥ ጳውሎስ ካነሣቸው ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

ሀ) ጳውሎስ የሞቱት ክርስቲያኖች ምን እንደሚገጥማቸው ያብራራል። ምንም እንኳን የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን አዲስ ብትሆንም፥ ከአባሎቻቸው አንዳንዶቹ በሞት የተለዩአቸው ይመስላል። ወይም ደግሞ የተሰሎንቄ አማኞች ጥያቄ ክርስቲያኖች በሚሞቱበት ጊዜ ምን ያጋጥማቸው ይሆን የሚለው ሊሆን ይችላል። ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ በሕይወት ያሉት አማኞች የሚያገኙዋቸውን በረከቶች ያጡ ይሆን? ጳውሎስ በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ በመመሥረት ለክርስቲያን ሞት ማለት ምን ማለት እንደሆነና የሞቱ ክርስቲያኖች ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ምን እንደሚያጋጥማቸው ያብራራል። ጳውሎስ አማኞች በታማኝነት በመመላለስ የክርስቶስን ምጽአት እንዲጠባበቁ ያበረታታቸዋል። ይህም ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ለሀፍረት እንዳይጋለጡ ይጠብቃቸዋል።

ለ) የሐሰት ትምህርቶችና ደብዳቤዎች በየአብያተ ክርስቲያናቱ ይሠራጩ የነበረ ይመስላል። እነዚህ የሐሰት ትምህርቶች ስለ ክርስቶስ ምጽአት የተሳሳቱ ሐሳቦችን ያስተላልፉ ነበር (2ኛ ተሰ. 2፡1–3)። የክርስቶስ ምጽአት እንደቀረበ በማሰብ አንዳንድ አማኞች ሥራዎቻቸውን አቁመው ይጠባበቁት ነበር። ጳውሎስ እነዚህ አማኞች ክርስቶስ የሚመጣበትን ጊዜ ከመገመት እንዲታቀቡ ይመክራቸዋል (2ኛ ተሰ. 2፡2)። ነገር ግን የጌታቸውን መመለስ በሚጠባበቁበት ጊዜ በታማኝነት ክርስቲያናዊ ጉዟቸውን እንዲቀጥሉና የዕለት ተግባሮቻቸውን እንዲያከናውኑ ያበረታታቸዋል።

ሐ) አንዳንድ አማኞች ደግሞ ክርስቶስ ቀደም ብሎ እንደ ተመለሰና እነርሱ ግን ሳያገኙት እንደ ቀሩ ያስቡ ነበር። ለእነዚህ አማኞች ጳውሎስ የክርስቶስ ምጽአት በሚደርስበት ጊዜ ሁኔታዎች ምን እንደሚመስሉና ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ደግሞ ሐሳዊ መሢሕ መገለጥ እንዳለበት ይናገራል። ጳውሎስ ከየትኞቹም መልእክቶቹም በበለጠ ስለዚህ ክፉ መሪ በዚህ የተሰሎንቄ መልእክት ውስጥ በሰፊው ያብራራል። ጳውሎስ ይህንን መሪ የዐመፅ ሰው ሲል ይጠራዋል።

መ) ወንጌሉን ለመቀበል በማይፈልጉት ሰዎች ላይ አንድ ቀን የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚመጣ በመግለጽ ጳውሎስ በስደት ውስጥ የነበሩትን ክርስቲያኖች ለማበረታታት ፈለገ። በክርስቶስ ለማመን ለማይፈልጉና በአማኞች ላይ ስደትን የሚያመጡ ሰዎች አንድ ቀን ለዘላለማዊ ቅጣት ይጋለጣሉ። በታማኝነት የጸኑ አማኞች ግን ሽልማትንና የዘላለም ሕይወትን ያገኛሉ።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ፡– እነዚህን እውነቶች ማወቅ ለክርስቲያኖች ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድን ነው? |

<u>3ኛ ዓላማ</u>፡ አማኞች ከወሲባዊ ኃጢአቶች ራሳቸውን እንዲጠብቁ ለማበረታታት? (1ኛ ተሰ. 4፡1–8)

<u>4ኛ ዓላማ</u>፡– በተሰሎንቄ የነበሩት አይሁዶች ጳውሎስ ገንዘብን ብቻ እንደሚፈልግና ለተሰሎንቄ አማኞች ምንም ዓይነት ፍቅር እንዳልነበረው

በመግለጽ ስሙን ያጠፉ የነበረ ይመስላል። እነዚህ ከሳሾች ጳውሎስ ምንም ዓይነት መለኮታዊ የሐዋርያነት ሥልጣን እንዳልነበረው ይናገሩ ነበር። ይህ አዳዲስ አማኞችን ግራ ሊያጋባቸው ስለሚችል በአንደኛ ተሰሎንቄ ውስጥ ስለ ሐዋርያዊ አገልግሎቱ እነርሱን ለማገልገል ስላነሣሣው ፍላጎት ያብራራል።

## የ1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ ልዩ ባሕርያት

1) በ1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቶች ውስጥ ስለ መጨረሻው ዘመን ብዙ ትምህርቶችን እናገኛለን። እንዲያውም ከ2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቶች ውስጥ አንድ ሦስተኛው ክርስቶስ ሊመለስ ሲል ስለሚሆኑት ሁኔታዎች የሚያብራራ ነው።

2) እነዚህ ጳውሎስ ከጻፋቸው መልእክቶች ሁሉ ቀዳሚዎቹ ናቸው። ምናልባትም ከእነዚህ መልእክቶች በፊት የተጻፈው የገላትያ መልእክት ሊሆን ይችላል።

## የ1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቶች አስተዋጽኦ

**1ኛ ተሰሎንቄ፡-** ከሌሎቹ መልእክቶቹ በተለየ ሁኔታ ጳውሎስ በዚህ መልእክት ውስጥ መጀመሪያ አስተምህሯዊ ቀጥሎ ደግሞ ተግባራዊ አኗኗርን አላሰፈረም። ነገር ግን 1ኛ ተሰሎንቄ በሚከተሉት ሁለት ክፍሎች ተከፍሏል፡-

1. ጳውሎስ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖችን እምነትና ከእነርሱ ጋር የነበረውን ግንኙነት ይከልሳል (1ኛ ተሰ. 1–3)።

   ሀ. ጳውሎስ ስለ ተሰሎንቄ አማኞች እግዚአብሔርን ያመሰግናል (1ኛ ተሰ. 1)።

   ለ. ጳውሎስ አማኞቹ ምሳሌያዊ ሕይወት እንዲኖሩ ያሳስባቸዋል (1ኛ ተሰ. 2)።

   ሐ. ጳውሎስ የጢሞቴዎስን ዘገባ (ሪፖርት) ከሰማ በኋላ ደስ መሰኘቱን ይገልጻል (1ኛ ተሰ. 3)።

2. ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች የክርስቶስን ምጽአት እየተጠባበቁ እንዴት ሊመላለሱ እንደሚገባ ያሳስባቸዋል (1ኛ ተሰ. 4–5)።

   ሀ. ጳውሎስ አማኞች የተቀደሰ የፍቅርና የሰላም ሕይወት እንዲመሩ ያሳስባቸዋል (1ኛ ተሰ. 4፡1–12)።

   ለ. ክርስቶስ በድንገት ሲገለጥ የሞቱ አማኞች ምን እንደሚሆኑ ያብራራል (1ኛ ተሰ. 4፡13–5፡12)።

   ሐ. ጳውሎስ አማኞች መሪዎቻቸውን እንዲያከብሩ ይመክራቸዋል (1ኛ ተሰ. 5፡12–28)።

## 2ኛ ተሰሎንቄ፡—

1. ጳውሎስ አሳዳጆቻቸው ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ፍርድን እንደሚቀበሉ በመግለጽ በመከራ ውስጥ ያሉትን አማኞች ያበረታታቸዋል (2ኛ ተሰ. 1)
2. ጳውሎስ የዐመፁ ሰው ሳይገለጽ ክርስቶስ እንደማይመለስና አማኞች በታማኝነት ሊኖሩ እንደሚገባ ያብራራል (2ኛ ተሰ. 2)።
3. ጳውሎስ አማኞች የክርስቶስን መመለስ ሲጠባበቁ ክርስቶስን በትጋት እንዲያገለግሉ ያሳስባቸዋል (2ኛ ተሰ. 3)።

## ሁለተኛ ቀን 1ኛ ተሰሎንቄ 1–5

ገብረ እግዚአብሔር በክርስቶስ ካመነ ብዙም ሳይቆይ እናቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች። እናቱም እንደ እርሱ አዲስ አማኝ ነበረች። ገብረ እግዚአብሔር እናቱን ከልቡ ይወዳት ስለነበር ልቡ በኀዘን ቆሰለ። አሁን ምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ይሆን ያለችው ሲል አሰበ። በሥቃይ ርዶ ድምፁን ጮኸ አድርጎ አለቀሰ። ሌላ ክርስቲያን ሲያለቅስ ሰምቶት ክርስቲያኖች ሊያለቅሱ አይገባም ሲል በብርቱ ገሠጸው። የገብረ እግዚአብሔር ዘመዶች በአብዛኛው ክርስቲያኖች ባለመሆናቸው እናቱ ጥንታዊ ልማዶች በሚጠይቁት መንገድ እንድትቀበር የግድ አሉ። ምንም እንኳን ገብረ እግዚአብሔር እናቱ በክርስቲያናዊ መንገድ እንድትቀበር ቢፈልግም፥ ለዘመዶቹ ሲል በባህላዊ መንገድ እንድትቀበር አደረገ። ይህም ባህላዊ የአቀባበር ሥርዓት ድምፅን ጮኸ አድርጎ ማልቀስን፥ ደረት መምታትንና፥ ከፊት ላይ ጭቃ መለጠፍን እና ሌሎችንም ተመሳሳይ ተግባራትን ይጨምር ነበር።

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ፡— ሀ) ለክርስቲያኖች የምንወዳቸው ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ ምን ዓይነት ምላሽ መስጠት እንዳለብን እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀውን ነገር ማወቁ ለምን ያስፈልጋል? ለ) እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች እንደ አማኞች በምንሞትበት ጊዜ የምናገኘውን ተስፋ ማወቁ ለምን ያስፈልጋል? ሐ) አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ በማልቀስ (ክርስቶስ እንዳደረገው ዮሐ. 11፡35 አንብብ) እና ዛሬ ብዙ ሰዎች እንደሚያደርጉት በከንቱ በመጮህ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? |

ሞት ለአማኞችም ሆነ ለማያምኑ ሰዎች የማይቀር ነገር ነው። ሞት ወደዚህ ዓለም የመጣው አዳምና ሔዋን መጀመሪያ ኃጢአት በሠሩበት ጊዜ ሲሆን እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ የሚቀጥል ይሆናል። የኋላ ኋላ ግን ክርስቶስ ሞትን ያስወግደዋል (ራእ. 21፡4)። ክርስቲያኖችና ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች በሚሞቱበት ጊዜ ምን እንደሚከሠት ማወቁ ለአማኞች በጣም አስፈላጊ ነው። ጳውሎስ ከተሰሎንቄ አማኞች ጋር ጥቂት ጊዜ ብቻ እንዳሳለፈ ስደት በመከሠቱ ስፍራውን ለቅቆ ለመሄድ ተገድዶ ነበር። የተሰሎንቄ አማኞች ካልተማሯቸው ነገሮች አንዱ የአማኞች ሞትና ያም ሞት ከክርስቶስ መመለስ ጋር የሚዛመድበት ሁኔታ ነበር። ጳውሎስ ከተሰሎንቄ ከተሰናበተ በኋላ አንዳንድ ክርስቲያኖች በሞት የተለዩ ይመስላል። በዚህን ጊዜ የተሰሎንቄ አማኞች «የምንወዳቸውን ወገኖች እንደገና እናያቸው ይሆን? ከሞት በኋላ ተስፋና ሕይወት አለን? የሞቱት

አማኞች የክርስቶስን ክብርና የንግሥና በረከት አያገኙም ማለት ነውን? የሞቱ ወገኖቻችንን በምንቀብርበት ጊዜ ጥንታዊውን ባህል መከተል አለብን ወይስ የተለየ ነገር ማድረግ አለብን?» እነዚህና ሌሎችም ጥያቄዎች የተሰሎንቄን አማኞች ያስጨንቋቸው ነበር። ጳውሎስ ሞት ለአማኞች የተለየ ነገር መሆኑን ይናገራል። ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የተነሣ አማኞች ከሞት እንደሚነሡ ዋስትና ተሰጥቷቸዋል። ስለሆነም ሞትን መፍራት የለብንም። መሞት ወይም ከሥጋ መለየት ማለት ከጌታ ጋር መሆን ማለት ነውና። በሞት የተለዩን ወንድሞቻችን የክርስቶስን የንግሥና በረከት ሳያገኙ ይቀሩ ይሆን? ለሚለው የተሰሎንቄ አማኞች ፍርሃት ጳውሎስ አጥጋቢ ምላሽ ሰጥቷል። ጳውሎስ እንዳብራራው የሞቱት አማኞች በሕይወት ያሉት አማኞች ከመለወጣቸው አስቀድመው ከሞት እንደሚነሡና በቀዳሚነት የበረከቱ ተካፋዮች እንደሚሆኑ አስረድቷል። ከዚህም ተስፋ የተነሣ የክርስቲያኖች የቀብር ሥነ ሥርዓት ተስፋ ቢስነት የሚታይበት ጊዜ ሊሆን አይገባም። ይህ ጊዜ የክርስቶስን የትንሣኤ ተስፋ የሚፈነጥቅ ሊሆን ይገባል። ለዚህ ነው ጳውሎስ ተስፋ እንደሌላቸው ዓለማውያን አናዝንም የሚለው። የምናለቅሰው ለጊዜው ከወገኖቻችን በመለየታችን ብቻ ነው። ይህም አንድ ሰው ወደ አሜሪካ ወይም ወደ ሌላ ቦታ በሚሄድበት ጊዜ እንደምናዝን ማለት ነው።

---

8ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ተሰ. 1-3 አንብብ። ሀ) በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ ክርስቶስ ምጽአት የተጠቀሱትን እውነቶች ዘርዝር። ለ) ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች ክርስቶስን በሚያስከብር መልኩ እንዴት ሊመላለሱ እንደሚገባ አስተማረ።

---

## ጳውሎስ የተሰሎንቄን አማኞች እምነትና ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከለሰ (1ኛ ተሰ. 1-3)።

1) ጳውሎስ ስለ ተሰሎንቄ አማኞች እግዚአብሔርን ያመሰግናል (1ኛ ተሰ. 1)።

ሁለቱም የተሰሎንቄ መልእክቶች የሚጀምሩት በሦስት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰላምታ ነው። እነዚህም መሪዎች ከሦስት ወራት በፊት ወደ ተሰሎንቄ የክርስቶስን ወንጌል ያመጡ አገልጋዮች ነበሩ። የመልእክቱ ደራሲ ጳውሎስ ሲሆን፥ ሲላስና ጢሞቴዎስም አብረውት በቆሮንቶስ ነበሩ። ሁሉም አገልጋዮች ለሚወዷቸው አማኞች ሰላምታቸውን ልከዋል።

ጳውሎስ ከተሰሎንቄ አማኞች ጋር ያሳለፈው የአንድ ወር ወይም የስድስት ሳምንታት ጊዜ ሊዘነጋ የማይችል ነበር። ጳውሎስ ስለ ደኅንነታቸውና በስደት ውስጥ ለክርስቶስ ታማኞች ሆነው ስለ መጽናታቸው ከጢሞቴዎስ ሲሰማ ልቡ በምስጋና ተሞላ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። በመሆኑም ጳውሎስ እነዚህን አዳዲስ አማኞች በእምነታቸው ለማበረታታት ሲል መልእክቶቹን ጽፎአል።

ሀ) ጳውሎስ በሕይወታቸው ስለ ተከሠቱት ለውጦች የሰማውን አሳብ በመግለጽ አማኞቹን ያበረታታል። በተለይም በአማኞቹ ሕይወት ውስጥ የተከሠቱትን ሦስት ቀዳማይ ጉዳዮች ይዘረዝራል።

በመጀመሪያ፡- ከእምነት የተገኘ የሥራ ፍሬ ነበራቸው። ምንም እንኳ የሚያድነን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ማመናችን ቢሆንም፥ እግዚአብሔር እምነታችን ፍሬ እንዲያፈራ ይፈልጋል። እምነታችን አኗኗራችንን፥ አስተሳሰባችንንና አተገባበራችንን ይለውጠዋል። እምነታቸው የአእምሮ እውቀት ብቻ ሳይሆን፥ አኗኗራቸውን፥ በችግር ውስጥ ያሉትን ሰዎች የሚረዱበትን መንገድ፥ ወንጌሉን የሚመሰክሩበትን ሁኔታ፥ ወዘተ... ተቆጣጥሯል።

ሁለተኛ፡- የተሰሎንቄ አማኞች ተግባራቸውን ያከናወኑት በፍቅር ነበር። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን ይወዱትና እርስ በርሳቸውም ይዋደዱ ነበር። ፍቅር ስሜት ሳይሆን ተግባር ነው። ከዚህም ፍቅር የተነሣ የተሰሎንቄ አማኞች ለእግዚአብሔር ክብር ተግተው ሠርተዋል። በችግር ጊዜ በተለይም በከባድ ስደት ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ እርስ በርሳቸው ተረዳድተዋል።

ሦስተኛ፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመናቸው የመነጨ የተስፋ ጽናት ነበራቸው። በክርስቶስ እንዳመኑ ስደት ሲደርስባቸው በታማኝነት ጸንተው እንዲቆዩ ያደረጋቸው ምን ነበር? ተስፋቸው ነበር። ይህም ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣና እንደሚሸልማቸው መገንዘባቸው ነበር። ከዚህም የተነሣ የተሰሎንቄ አማኞች ስደትንና የተለያዩ ችግሮችን በታማኝነት ተጋፍጠዋል።

9ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እነዚህ ሦስት ነገሮች ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ለምን አስፈላጊዎች እንደሚሆኑ አብራራ። ለ) በሕይወትህ እነዚህ ሦስቱ ባሕርያት የሚገኙት እንዴት ነው?

ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች የተለወጠ ሕይወት፥ ከጣኦት አምልኮ የተመለሱበት ሁኔታና ኢየሱስ ክርስቶስን በማገልገል ምጽአቱን መጠበቃቸው በመቄዶኒያ ብቻ ሳይሆን በአካይያ ጭምር እንደታወቀ ያስረዳል። አካይያ ጳውሎስ በዚህ ጊዜ ወንጌሉን በሚሰብክበት በቆሮንቶስ ከተማ አካባቢ የምትገኝ ስፍራ ነበረች። ይህ ክርስቶስን ካወቁ የስድስት ወራት ዕድሜ ለነበራቸው አማኞች ምንኛ ታላቅ ምስክርነት ነው።

ለ. ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ጋር ስለነበራቸው ልዩ ግንኙነት በመመስከር አማኞችን ያበረታታል። ጳውሎስ የመረጣቸው እግዚአብሔር የተሰሎንቄን አማኞች እንደሚወዳቸው ገልጾአል። ከደረሰባቸው ስደትና ችግር ባሻገር፥ እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወዳቸው ማስታወስ ያስፈልጋቸው ነበር።

ወንጌል መጀመሪያ ወደ ተሰሎንቄ ሲመጣ ከእግዚአብሔር የመነጨ እንጂ ከንቱ ተስፋ እንዳልሆነ በሚያረጋግጥ መልኩ በታላቅ ኃይል ነበር የተገለጠው። ወንጌል ወደ ተሰሎንቄ አማኞች የመጣው በቃላት ብቻ አይደለም። ጳውሎስ በመካከላቸው ወንጌሉን በመኖር መልካም ምሳሌ ሆኗቸው ነበር። ይህ ማለት ግን ክርስቶስን ለመከተል የደረሱበት ውሳኔ ቀላል ነበር ማለት አይደለም። አይሁዶች በጳውሎስ ላይ ስደትን እንዳደረሱ ሁሉ በተሰሎንቄ አማኞች ላይም አይሁዶችና አሕዛብ ከፍተኛ ስደት በማስከተል ላይ ነበሩ። ነገር ግን በቶሎ ይመጣል ብለው በሚያምኑት በክርስቶስ ላይ ጽኑ እምነት ስለነበራቸው በእምነታቸው ጸንተው ቆመዋል።

2) ጳውሎስ ለአማኞች ስለ ሕይወቱ ምሳሌነት ያስታውሳቸዋል (1ኛ ተሰ. 2)።

የጳውሎስ አገልግሎት በተሳሳተ ፍላጎት የተሞላ ነው የሚሉ ከሳሾች ሳይነሡ አልቀሩም። አንዳንድ ሰዎች ጳውሎስ ሰዎችን ለማስደሰት እንደሚሞክርና ገንዘብ የመሰብሰብ ዓላማ እንዳለው ለተሰሎንቄ አማኞች ሳይናገሩ አልቀሩም። በመሆኑም ጳውሎስ እነዚህ ክሶች እውነት ሊሆኑ የማይችሉባቸውን ምክንያቶች ይዘረዝራል።

ሀ) ጳውሎስ በተሰሎንቄ ከመቆየት ያገኘው ነገር ቢኖር ተጨማሪ ቁሳቁስ ሳይሆን ስደትን ነበር። ከስደቱ ሥቃይ ባሻገር ጳውሎስ የወንጌል ስብከት አገልግሎቱን ቀጥሏል።

ለ) በሚሰብኩበት ጊዜ ትምህርታቸውን ለማሳየት ከሚፍጨረጨሩት የሃይማኖት ሊቃውንት በተቃራኒ፥ ጳውሎስ መልእክቱ ቀላል እንደነበረ ያስረዳል። ዓላማውም ሰዎችን ማስደነቅ ሳይሆን እውነትን በግልጽ ማብራራት ነበር።

ሐ. ሰዎች ገንዘብ እንዲከፍሏቸው ከሚያስገድዱ ሌሎች የሃይማኖት መሪዎች በተቃራኒ፥ ጳውሎስ ከተሰሎንቄ አማኞች ምንም ገንዘብ እንዳልተቀበለና የራሱን የኑሮ ወጪ ለመክፈል በእጆቹ ተግቶ ይሠራ እንደነበር ያስረዳል።

መ. ጳውሎስ ሲላስና ጢሞቴዎስ የግል ሕይወታቸውን በመጠበቅ፥ *በቅድስና፥ በጽድቅና እንከን በሌለው ሕይወት* እንደ ተመላለሱ ያስረዳል። አንድ ጊዜም የተሰሎንቄን ሕዝብ በማታለል ወይም በማጭበርበር ሊጠቀሙባቸው አልሞከሩም ነበር።

ጳውሎስ አገልግሎቱን ካቀረበበት ሁኔታ የተነሣ የተሰሎንቄ አማኞች በክርስቶስ ባመኑ ጊዜ በጳውሎስ ላይ ጥገኞች አልሆኑም። ነገር ግን በእግዚአብሔርና በደኅንነት ስጦታው፥ ብሎም በጥበቃው ላይ ተደግፈዋል።

ሠ. ጳውሎስ የተሰሎንቄን አማኞች ከመተው ይልቅ ከልቡ ያፈቅራቸውና ብዙ ጊዜ ወደ ተሰሎንቄ ተመልሶ የተቋረጠ አገልግሎቱን ለመቀጠል ሲሞክር ቆይቷል። ነገር ግን ሰይጣን ከልክሎታል። ሰይጣን ጳውሎስን እንዴት እንደ ከለከለው አልተገለጸም። ምናልባትም ጳውሎስ ይህን ሲል የአይሁዶች ተቃውሞ መቀጠሉንና ወደ ተሰሎንቄ ተመልሶ ቢመጣ እዚያ በሚገኙት አማኞች ላይ ተጨማሪ ስደት ሊያስከትል መቻሉን ለማመልከት ይሆናል። ጳውሎስ ይህንን ለማድረግ ስላልፈለገ ወደ ተሰሎንቄ ሳይሄድ ቀርቷል። ጳውሎስ ከአይሁዶች ስደት በስተጀርባ የሰይጣን እጅ እንደ ነበረበት ለመመልከት ችሎ ነበር።

---

10ኛ ጥያቄ፡- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከአባሎቻቸው ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ከጳውሎስ ምን እንማራለን። አንዳንድ ጠቃሚ ነጥቦችን ዘርዝር።

---

3. ጳውሎስ የጢሞቴዎስን ሪፖርት ከሰማ በኋላ የተሰማውን ደስታ ይገልጻል (1ኛ ተሰ. 3)።

ጳውሎስ የተሰሎንቄን አማኞች አኗኗር ለማወቅ የወሰዳቸውን እርምጃዎች የፍቅሩ መግለጫ አድርጎ ይጠቅሳል። ከደረሰባቸው ስደት የተነሣ እምነታቸውን እንዳይተዉ ሰግቶ ነበር። ይህንንም ለማጣራት ጢሞቴዎስን ወደ ተሰሎንቄ ላከው። ጢሞቴዎስ ጳውሎስ ወደሚያገለግልበት የተሰሎንቄ ከተማ በተመለሰ ጊዜ፥ ከስደቱ ባሻገር የተሰሎንቄ አማኞች በክርስቶስ ማመናቸውን እንደቀጠሉና ታላቅ ፍቅርም እንደነበራቸው ለጳውሎስ አብራራ። ይህ ጳውሎስን እጅግ በማስደሰቱ እነርሱን ለማየት የነበረውን ጉጉት አናረው። ጳውሎስ ስደትን ተቋቁሞ መዝለቅ በዋናነት የሰዎች ጥረትና ችሎታ ሳይሆን የእግዚአብሔር የማስቻል ውጤት እንደሆነ ይገነዘብ ነበር። ስለሆነም እግዚአብሔር የተሰሎንቄን አማኞች ልብ እንዲያበረታ፥ እንዲያጸናቸውና እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት ድረስ ቅዱሳን አድርጎ እንዲጠብቃቸው ይጸልያል።

ብዙውን ጊዜ ስደት በሚደርስብን ጊዜ ምን እንደምናደርግ እናስባለን። ለክርስቶስ የተሰጠ ሕይወት መኖራችንን ለማመልከት ሕይወታችንን መመርመሩ ጠቃሚ ነው። ነገር ግን ስደት በሚመጣበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደማይተወን መረዳት አለብን። እርሱ ከእኛ ጋር በመሆን ፈተናውን እንድንቋቋምና ጸንተን እንድንቆም ይረዳናል።

> 11ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከእምነትህ የተነሣ የተሰደድክበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) በዚህ ጊዜ ለክርስቶስ ታማኝ ሆኖ ስለ መጽናት ምን ተማርክ? ሐ) ለአማኞች እግዚአብሔር በስደት ጊዜ በእምነታቸው የሚጸኑበትን ኃይል እግዚአብሔር እንደሚሰጣቸው መረዳቱ ምን ይጠቅማል?

## ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች የክርስቶስን የቅርብ ቀን ምጽአት እየተጠባበቁ እንዴት ሊመላለሱ እንደሚገባ ያስተምራቸዋል (1ኛ ተሰ. 4–5)።

> 12ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ተሰሎንቄ 4–5 አንብብ። ሀ) ጳውሎስ በመጨረሻው ዘመን ስለሚሆነው ነገር ያስተማራቸውን እውነቶች ዘርዝር። ለ) እግዚአብሔርን በሚያስደስት መንገድ ለመኖርና ለክርስቶስ ምጽአት ለመዘጋጀት ከፈለግን ልናደርጋቸው የሚገቡን ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

ጢሞቴዎስ ለጳውሎስ ስለ ተሰሎንቄ አማኞች ጽናት በገለጸ ጊዜ፥ አንዳንድ አሳሳቢ ጉዳዮች እንደነበሩም መናገሩ አልቀረም። ጳውሎስ በዚህ የአንደኛ ተሰሎንቄ የመጨረሻ ክፍል ውስጥ እነዚህን ጉዳዮች ይዳስሳል። የጳውሎስ ቀዳማዊ ዓላማ አማኞች እግዚአብሔርን በሚያስደስት መልኩ እንዲኖሩ ነበር።

1) ጳውሎስ አማኞች የተቀደሰ፥ በፍቅር የተሞላና ሰላማዊ ሕይወት እንዲኖሩ ያበረታታቸዋል (1ኛ ተሰ. 4፡1–12)።

እግዚአብሔር ባዳነን ጊዜ ከኃጢአት ብቻ ነፃ አላወጣንም። እርሱ እንቀደስ ዘንድ አድኖናል።

> 13ኛ ጥያቄ፡- መቀደስ ማለት ምን ማለት ነው? ይህን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ አንብብ።

የመቀደስ መሠረታዊ ፍች መለየት ማለት ነው። በክርስቶስ አምነን በምንድንበት ጊዜ እንደ ተቀደስን ቢገለጽም፥ እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ የፈጸመውን ተግባር በሚያንጸባርቅ መልኩ የተቀደሰ ሕይወት እንድንኖር ይፈልጋል። ዛሬ እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ከሚፈጽማቸው ነገሮች አንዱ ባለማቋረጥ እኛን ቅዱሳን ማድረግ ነው። የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዓላማ ከክርስቶስ ጋር በምንገናኝበት ጊዜ እንድንከብርና የክርስቶስን ያህል ቅድስና እንዲኖረን ነው (1ኛ ዮሐ. 3፡2)።

ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች አጽንኦት ሊሰጡ የሚገባቸውን የተለያዩ የክርስቲያናዊ አኗኗር ገጽታዎች ይዳስሳል።

ሀ) <u>ወሲባዊ ንጽሕና</u>፡- ልክ እንደኛው የተሰሎንቄ አማኞችም ከወሲባዊ ንጽሕና ጋር የተያያዙ ችግሮች ነበሩባቸው። ቀደም ሲል በጣኦት አምልኳቸው ውስጥ ብዙውን ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ጋር ወሲባዊ ግንኙነቶችን ይፈጽሙ ነበር። ወደ ክርስትና ሕይወት ሲመጡ ይህንኑ ልምምድ ማቆሙ ቀላል አልሆነላቸውም። ጳውሎስ ግን ሰውነታቸውን ለመቆጣጠርና በንጽሕና ለመመላለስ ቁርጥ ውሳኔ እንዲያደርጉ ያበረታታቸዋል። ዛሬ ይህንን ትምህርት የማይታዘዝና ሌሎችም ንጹሕ ሕይወት እንዳይኖሩ የሚያስተምር ማንም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጧል። ይህም እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ የሰጠውን የመንፈስ ቅዱስ ድምጽ አለመስማትና አለማክበር ይሆናል። እግዚአብሔርን የሚያሳስበው ከግል ሕይወታችን ይልቅ እርሱን የምናመልክበት ሁኔታ ነው ብለን የምናስብ ከሆነ ተሳስተናል። አንዳንድ አማኞች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደሚያስተምሩት እግዚአብሔር ለወሲባዊ ንጽሕናችን ግድ እንደሌለው የሚያሳይ ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም። ቅድስናና ንጽሕና በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። ከጋብቻ ግንኙነት ውጪ የሚፈጸም ማንኛውም ወሲብ በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ኃጢአት ነው። የወሲቡን ተግባር የምናጋራውም ሰው የዚሁ በደል ተካፋይ ይሆናል።

ለ) <u>የፍቅር ግንኙነቶች</u>፡- የተሰሎንቄ አማኞች ቀደም ሲል ያደርጉ እንደነበረው ለእርስ በርሳቸው የነበራቸውን ፍቅርና መተሳሰብ አጽንተው ሊይዙ ይገባ ነበር።

ሐ) <u>ተግቶ መሥራት</u>፡- አማኞች ተግተው ሊሠሩና የጭምትነት ሕይወት ሊኖሩ ይገባቸው ነበር። ይህም ለሌሎች የሚሆን ምሳሌያዊ ሕይወት ለመኖር ያስችላቸዋል። የተሰሎንቄ አማኞች ክርስቶስ ቶሎ ይመለሳል ብለው በማሰባቸው ይመስላል ተግተው ከመሥራት ይቆጠቡ ነበር። ከዚህም የተነሣ የኢኮኖሚ ችግሮችን ለመጋፈጥ ተገደዱ። ይህም ብቻ አልነበረም። እርስ በርሳቸው በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ለመግባትና ኃጢአትን ለመሥራት ተገድደዋል። ስለሆነም ጳውሎስ ወደ ሥራቸው እንዲመለሱና ሰዎች ክርስቲያኖችን ያከብሯቸው ዘንድ ምሳሌያዊ ሕይወት እንዲኖሩ ያበረታታቸዋል። ብዙ ሰዎች ሥራ ክፉ ነው የሚል ባሕላዊ አመለካከት አላቸው። ስለሆነም ብዙ ወጣቶች ወደ ትምህርት ቤት መሄድ ከጀመሩ በኋላ በቤት ተገቢውን ሥራ ከማከናወን ይቆጠባሉ። የእርሻም ሆነ ሌሎች ማናቸውንም ሥራዎች ከማከናወን ይሰንፋሉ። ጳውሎስ ይህንን ሲል

ከትምህርት ደረጃችሁ ጋር የሚመጣጠን ሥራ ካገኛችሁ ማለቱ አልነበረም። ይልቁንም ማንም ሰው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቀም ቢሆን ያገኘውን ሥራ ማከናወን እንዳለበት ያስገነዝባል። ይህ ለሌሎች ጥሩ ምሳሌ በመሆኑ የክርስቶስን ስም ያስከብራል።

14ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እነዚህን ሦስት እውነቶች ለወጣቶች ማስተማር አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) ብዙ ወጣቶች ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ትናንሽ ሥራዎችን የማይሠሩት ለምንድን ነው? ሐ) ዛሬ ጳውሎስ በኢትዮጵያ ላሉት ወጣቶች ደብዳቤ የሚጽፍ ቢሆን ኖሮ ክርስቶስን ስለሚያስከብር ሕይወት ምን ዓይነት ተግባራዊ ነጥቦችን ይጠቅስላቸው ነበር።

2) ጳውሎስ ክርስቶስ በድንገት በሚመለስበት ጊዜ የሞቱት አማኞች ምን እንደሚሆኑ ያብራራል (1ኛ ተሰ. 4፡13-5፡12)።

ጢሞቴዎስ የተሰሎንቄ አማኞች ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ የሞቱ አማኞች ምን እንደሚሆኑ ያነሷቸውን ጥያቄዎች ለጳውሎስ አቀረበ። ምንም እንኳ ጳውሎስ ተሰሎንቄን ከለቀቀ ከሦስት ወራት ባይበልጥም ቢያንስ አንድ ክርስቲያን በሞት የተለያቸው ይመስላል። ይህ ደግሞ የተሰሎንቄ አማኞች የሞቱ ክርስቲያኖች በተለይም ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ምን እንደሚሆኑ እንዲያስቡ አደረጋቸው። ለሁሉም ክርስቲያኖች ስለዚሁ ጉዳይ ጥርት ያለ አሳብ መያዙ በጣም አስፈላጊ ነው። ጳውሎስ ካስተማራቸው ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

ሀ) ሞት ለክርስቲያን እንደ እንቅልፍ ነው። አንድ ሰው ማታ ወደ አልጋው እንደሚሄድና ከብዙ ሰዓታት በኋላ እንደሚነቃ ሁሉ፥ አንድ አማኝ በሚሞትበት ጊዜ ነገር ዓለሙ ጨለመ ማለት አይደለም። ምክንያቱም አንድ ቀን ሥጋዊ አካላችን ከሞት ይነሣልና። (መንፈሳችን አይሞትም፥ ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ይቆይና በትንሣኤ ከሰውነታችን ጋር እንደገና ይዋሃዳል።) ሞቶ የተነሣውን የክርስቶስ ኢየሱስን ምሳሌነት በመከተል እኛም ከሞት እንነሣለን። በመሆኑም ሞትን እንደ መጨረሻ ነጥብ አድርገን በመመልከት ልንፈራ አይገባም።

ለ) አማኞች ሁሉ ለዘላለም ሕይወት እንደሚነሡ ከሚያስረዳው የተስፋ ቃል የተነሣ ክርስቲያኖች ለሞት የተለየ አመለካከት ሊኖራቸው ይገባል። ሞት እዚህ በምድር ላይ ከሚያመጣው መለየት የተነሣ ኀዘንና ሥቃይ ቢኖርም፥ የዓለማውያን ዓይነት ተስፋ ቢስነት ሊሰማን አይገባም። በመሆኑም አንድን አማኝ በምንቀብርበት ጊዜ ተስፋ ቢስነት ሊሰማን አይገባም። ይህ ማለት ግን ለሞተ ሰው ማልቀስ ትክክል አይደለም ማለት አይደለም። ምክንያቱም ክርስቶስ እንኳን አልዓዛር በሞተ ጊዜ አልቅሷልና (ዮሐ. 11፡35)። እዚህ ጋር ጳውሎስ የሚነቅፈው ተስፋ በመቁረጥ ሰዎች ከመጠን በላይ ማልቀሳቸውን ነው።

ሐ) የሞቱ አማኞች በክርስቶስ የወደፊት ግዛት ውስጥ የሚገለጡትን በረከቶች አያጡም። እንዲያውም ክርስቶስ ከሰማይ በሚመለስበት ጊዜ መጀመሪያ የሚያገኙት እነርሱ ናቸው። በትንሣኤ አካላቸው ከሞት ተነሥተው በእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ውስጥ ይኖራሉ። ከዚያ

በኋላ በሕይወት ያሉት አማኞች ይለወጣሉ። ይህም የሚሆነው ሰውነታቸው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለመኖር በሚያስችል መልኩ እንዲቀየር ነው። ከሞት የተነሡት አማኞችና የተለወጡት አማኞች ክርስቶስን በአየር ተቀብለው ከእርሱ ጋር ለዘላለም ይኖራሉ።

15ኛ ጥያቄ፡— ክርስቲያኖች በሙታን ትንሣኤ ማመናቸውን ተግባራዊ ቢያደርጉ ለሞት፥ ለስደትና ለተቀደሰ አኗኗር የሚኖራቸው አመለካከት እንዴት ይቀየራል?

አማኞች ለረጅም ጊዜያት ስለዚሁ ንጥቀትና ከመጨረሻው ዘመን አንጻር መቼ እንደሚፈጸም ሲከራከሩ ቆይተዋል። በራእይ ምዕራፍ 20 ከተገለጸው የክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት ጋር እንዴት ይዛመዳል። ስለ መጨረሻው ዘመን ክስተቶች ቅደም ተከተል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዚህ በግልጽ ተዘርዝሮ አንመለከተም። ከዚህም የተነሣ ክርስቲያኖች የተለያዩ አመለካከቶች አሏቸው። የአማኞችን መነጠቅ በተመለከተ ሁለት ዓበይት አተረጓጎሞች አሉ። ከእነዚህም አንዱ የተለያዩ አመለካከቶችን ያስተናግዳል።

1) ንጥቀትን ተከትሎ በራእይ 21–22 የተገለጸው የዘላለም መንግሥት ይቀጥላል። አንዳንድ ክርስቲያኖች በመጨረሻው ዘመን ክርስቶስ ልጆቹን ለመውሰድ ከሰማይ ይገለጣል። እርሱ የሞቱትን ያስነሣል። በሕይወት ያሉትን ደግሞ ይለውጣል። በዚህም ጊዜ በአዲስ ሰማይና ምድር ወዳለው ዘላለማዊ መንግሥቱ ይወስዳቸዋል። በዚህ ጊዜ የማያምኑ ሰዎች ከሞት ተነሥተው የክርስቶስን ፍርድ ይቀበላሉ። ከዚያም ወደ ዘላለማዊ ሲኦል ይወርዳሉ ብለው ያምናሉ።




2) የአማኞች መነጠቅ የክርስቶስን የሺህ ዓመታት መንገሥ አስቀድሞ የሚከሠት ይሆናል። አንዳንድ አማኞች በራእይ 20 ውስጥ የተገለጸው የክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት በራእይ 21–22 ከተገለጸው ዘላለማዊ መንግሥቱ እንደሚለይ ያስባሉ። እነዚህ አማኞች ክርስቶስ ምድራዊ አገዛዙን ሊጀምር ሲል ወደ ተከታዮቹ እንደሚመጣ ያስተምራሉ። በዚህን ጊዜ የሞቱ ክርስቲያኖች ይነሣሉ። በሕይወት ያሉትም ይለወጣሉ። ይህም በምድራዊ መንግሥት ላይ ከክርስቶስ ጋር እንዲገዙ ያስችላቸዋል። በእነዚህ አማኞች አመለካከት የዘላለም መንግሥት የሚጀምረው የሺህ ዓመቱ መንግሥትና የሰው ልጅ የመጨረሻ ዓመፅ ከተጠናቀቀ በኋላ ይሆናል። ነገር ግን የዚህ አመለካከት አራማጆች ይህ የክርስቲያኖች መነጠቅ መቼ እንደሚሆን ሦስት የተለያዩ አሳቦችን ያቀርባሉ።

በመጀመሪያ፡- ብዙ ክርስቲያኖች የአማኞች ንጥቀት ከክርስቶስ የምድር ላይ ንግሥና ጥቂት ቀደም ብሎ እንደሚፈጸም ያስባሉ። ክርስቲያኖች በታላቁ መከራ ውስጥ እንደሚያልፉና ብዙዎችም ለእምነታቸው እንደሚሞቱ ያምናሉ። ነገር ግን ክርስቶስ በሠራዊቱ ታጅቦ ከሰማይ ከመምጣቱ በፊት (ራእ. 19፡11-21 አንብብ)፥ በአየር ተገልጦ የሞቱትን አማኞች ያስነሣል፥ በሕይወት ያሉትንም ይለውጣል። እነዚህም አማኞች ከክርስቶስ ጋር ለመንገሥ ወደ ምድር ይመለሳሉ። የሚከተለው ሠንጠረዥ ይህንን አመለካከት ያብራራል።




ሁለተኛ፡- ጥቂት አማኞች ይህ ንጥቀት ታላቁ መከራ በሚባለው ጊዜ አጋማሽ ላይ እንደሚፈጸም ያስባሉ። እነዚህ አማኞች የታላቁን መከራ ዘመን በሁለት የሦስት ተኩል ዓመታት ክፍለ ጊዜያት ይከፍላሉ። አማኞች በመጀመሪያው የሦስት ተኩል ዓመታት የመከራ ጊዜያት ውስጥ እንደሚያልፉና ከሁለተኛው የሦስት ተኩል ዓመታት የታላቁ መከራ ጊዜ እንደሚተርፉ ያምናሉ። ይህም የሚሆነው ክርስቲያኖች በመነጠቃቸው ነው። ስለሆነም ከሦስት ተኩል ዓመታት በኋላ እነዚህ ከሞት የተነሡት አማኞች በምድር ላይ ለመንገሥ ከክርስቶስ ጋር ከሰማይ ይመጣሉ። ይህንን አመለካከት የሚያስረዳውን ሠንጠረዥ ከዚህ በታች ተመልከት።



ሦስተኛ፡- ሌሎች ብዙ አማኞች ክርስቲያኖች ከሰባት ዓመቱ ታላቅ መከራ በፊት ከዚህ ዓለም እንደሚወሰዱ ያምናሉ። ይህንንም የሚሉት በራእይ 3:10 ለፊልድልፍያ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን የተስፋ ቃል በመንተራስ ነው። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ነጥቆ እንደሚወስድና ከዚያ በኋላ በመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት የእግዚአብሔርን ፍርድ በምድር ላይ እንደሚያመጣ ያስተምራሉ። ከሰባት ዓመታት በኋላ ከክርስቶስ ጋር ወደ ምድር ተመልሰው ይገዛሉ። የሚከተለው ሠንጠረዥ ይህንን አመለካከት ያብራራል።




16ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከእነዚህ አመለካከቶች የትኛውን ታምናለህ? ለ) ቤተ ክርስቲያንህ ከእነዚህ አመለካከቶች የትኛውን ታምናለች? መልሱን ካላወቅህ ከቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች አንዱን ጠይቅ። ሐ) ክርስቶስ ሊወስድህ እንደሚመጣ፥ ሙታንን እንደሚያስነሣ፥ በሕይወት ያሉትን እንደሚለውጥና ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንደምንኖር መረዳቱ እነዚህ ክስተቶች መቼ እንደሚፈጸሙ ከመከራከር የበለጠ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

የተሰሎንቄ አማኞች ስለ መጨረሻው ዘመን ያነሡት ሌላም ጥያቄ ነበር። ክርስቶስ መቼ እንደሚመለስ ለማወቅ ፈልገው ነበር። አንዳንድ ሰዎች ክርስቶስ በቶሎ እንደሚመለስ ያስተምሩ ስለነበር አንዳንድ አማኞች ሥራቸውን ትተው ነበር። ጳውሎስ ይህንንም ጥያቄ በሁለት ዐበይት ነጥቦች አስደግፎ ይመልሳል፡-

ሀ) ክርስቶስ የሚመለስበት ጊዜ ድንገተኛና ያልተጠበቀ ስለሚሆን ጊዜው መቼ እንደሚሆን በትክክል ልናውቅ አንችልም። ይህ *ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ* ሁሉ ድንገተኛና ያልተጠበቀ ይሆናል። ክርስቶስ ሰዎች ባልጠበቁት ሰዓት ይመጣል። ይህም ማለት ክርስቶስ በዚህን ጊዜ ይመጣል ማለቱ ትክክል አይሆንም ማለት ነው። ክርስቶስ በዚህ ቀን ወይም ዓመት ይመጣል ልንል አንችልም።

ለ) የክርስቶስን መምጣት እየተጠባበቁ መኖር ማለት ዛሬ እንደሚመጣ ሆነን መኖር ማለት ነው። እርሱን ለማስከበር በታማኝነት እንኖራለን። አማኞች የብርሃን ልጆች በመሆናቸው ወይም የእግዚአብሔር የጽድቅ

መንግሥት ተካፋዮች በመሆናቸው፥ ከዓለም የተለየ ሕይወት መምራት ይኖርባቸዋል። ራሳችንን ልንቆጣጠር፥ በእምነት፥ በፍቅርና በተስፋ እየተመላለስን የክርስቶስን መምጣት መጠባበቅ ይኖርብናል። ከሁሉም በላይ በተስፋ ልንጸና ይገባል። ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ በሕይወት ብንኖር ወይም ብንሞት ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንደምንኖር እናውቃለን።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዓለማውያንና ሥጋዊ ክርስቲያኖች የሚያደርጓቸውንና ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ፍርድን የሚያስከትሉባቸውን ነገሮች ዘርዝር። ለ) ክርስቶስ በየትኛውም ጊዜ ሊመጣ እንደሚችል በሚያንጸባርቅ መልኩ እንደምንኖር ለማሳየት ልናደርጋቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ የማይኖሩት ለምን ይመስልሃል? ስለ ክርስቶስ ምጽአት እነዚህ ክርስቲያኖች የዘነጉት ነገር ምንድን ነው? |

3. ጳውሎስ አማኞች መሪዎቻቸውን እንዲያከብሩ ይመክራቸዋል (1ኛ ተሰ. 5፡12-28)።

ጳውሎስ በዚህ የማጠቃለያ ክፍል እያንዳንዱን የቤተ ክርስቲያን አባል የሚመለከቱትን ትእዛዛት ይዘረዝራል፡-

ሀ) የቤተ ክርስቲያን አባላት መሪዎቻቸውን ማክበር ይኖርባቸዋል። እነዚህ መሪዎች ምእመናንን ለመምራት ጊዜያቸውን የሚሰዉና የክርስቲያኖችን መንፈሳዊ ፍላጎቶች የሚያሟሉ ናቸው።

ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እርስ በርሳቸው በሰላም መኖር አለባቸው። በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ላይ ባላቸው የአመራር ኃላፊነት ክርስቲያኖች ተግተው እንዲሠሩ ሊያበረታቱና ራሳቸው ስደትን ለመጋፈጥና ለክርስቶስ ለመመስከር ቆራጦች ሊሆኑ ይገባል። በመንጋዳት ላይ ያሉትን አማኞች ሊንከባከቡና ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ክብር ለመኖር በሚጥሩበት ወቅት ሊረዱቸው ይገባል። ክርስቲያኖች በሚያሳድዳቸው ዓለማውያንና በሌሎችም ሰዎች ላይ ቂም ሊይዙ ይችሉ ነበር። መሪዎች አማኞች እንዲህ ዓይነቱን የመራርነትና የበቀል ስሜት እንዲያስወግዱ በማስተማር ይረዱቸዋል። ክርስቲያን መሪዎች ሰዎች የሚዋደዱበትንና እርስ በርስ የሚተጋገዙበትን ድባብ የመፍጠር ኃላፊነት ተጥሎባቸው ነበር።

ሐ) ከእግዚአብሔር ጋር የሚመላለሱ አማኞች ሁሉ የሚከተሉት ባሕርያት ይኖራቸዋል፡-

1.በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ደስ መሰኘት። እግዚአብሔር ምንጊዜም ባስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንደማንገባ ቃል አልገባልንም። ነገር ግን ስደትና አስቸጋሪ ሁኔታዎች በሚገጥሙን ጊዜ ከእኛ ጋር አብሮ እንደሚሆን ቃል ገብቶልናል። የትኛውም ችግር ከምንቋቋመው በላይ እንዳልሆነ እያሳየን በችግሩ ውስጥ ያሳልፈናል (1ኛ ቆሮ. 10፡13 አንብብ)። እግዚአብሔር ወደ ሕይወታችን የሚመጣው ነገር ሁሉ በእርሱ ፈቃድ እንደሚፈጸምና ይህም በመንፈሳዊ ሕይወታችን በሳሎች እንድንሆን የሚያግዘን መሆኑን ያስረዳል።

2. አማኞች ለማንኛውም ሁኔታ ጸሎትን ቀዳሚ ምላሻችን ልናደርገው ይገባል።

3. አማኞች የትንቢትን ስጦታ ቸል ማለት የለባቸውም። የሐሰት ትንቢትን በሚናገሩ ሰዎች ላይ ቤተ ክርስቲያናቸውን ከእውነት በሚያርቁ ሰዎች ሳቢያ የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ትንቢት እንዳይነገር የከለከለች ይመስላል። ወይም ደግሞ ነቢያትን የማክበርና ትምህርታቸውን የመስማት ፍላጎት አልነበራቸውም። ጳውሎስ ግን ይህን የእግዚአብሔር ስጦታ የምናስተናግደው በዚህ መንገድ እንዳልሆነ ያስረዳል። እግዚአብሔር የሰጠንን አንድ ነገር ለመቀበል ፈቃደኞች በማንሆንበት ጊዜ የመንፈስን እሳት ማጥፋታችን ነው። ስለሆነም የተሰሎንቄ አማኞች የትንቢትን ስጦታ መፍቀድ ያስፈልጋቸው ነበር። ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች ሁሉንም እንዲመረምሩና መልካሙን እንዲይዙ ያበረታታቸዋል። ለመሆኑ አንድ ትንቢት ከእግዚአብሔር መሆን አለመሆኑን የምንፈትነው እንዴት ነው። በዚህ ረገድ ልንጠቀም የምንችላቸው አምስት መሣሪያዎች አሉ።

<u>በመጀመሪያ</u>፥ ይህ ትንቢት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሰው አሳብ ጋር ይስማማል ወይ? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። የተሰሎንቄ አማኞች አንዳንድ የሐሰት ነቢያት ክርስቶስ በዚህ ቀን ይመጣል ባሏቸው ጊዜ ይህንን ጥያቄ ለማንሣት ባለመቻላቸው ሥራቸውን አቁመዋል። ክርስቶስ እኔ የምመጣበትን ቀን ማንም አያውቅም ሲል የተናገረውን ዘንግተው ነበር (ማቴ. 24፡36)።

<u>ሁለተኛ</u>፥ ይህ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገትና እውቀት ጠቃሚ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ማንሣት። መንፈሳዊ ጠቀሜታ የሌላቸው ትንቢቶች አሉ። አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የትንቢት ቃል አለ ወይ ብሎ በጠየቀ ጊዜ አንድ ሰው ብድግ ብሎ ሃሌሉያ እያለ ደጋግሞ ይጮህ ጀመር። በዚህ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩት ሰዎች በሙሉ እልል አሉ። በመሠረቱ ይህ የትንቢት ቃል አይደለም። ይህ ለትምህርትም ሆነ ሕዝቡን ለማነጽ የማይጠቅም የቃላት ድግግሞሽ ነው። የዚህ ዓይነቱ ትንቢት ማንንም ወደ እግዚአብሔር አያስጠጋም።

<u>ሦስተኛ</u>፥ ትንቢቱን የሚናገረው ግለሰብ ባሕርይ ነው። እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ቃሉን ለማስተላለፍ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለና ለቃሉ የሚታዘዝ ሰው ይጠቀማል። ነገር ግን ትንቢቱን የሚናገረው ግለሰብ በኃጢአት የሚመላለስ ከሆነ ወይም ደግሞ ትንቢቱ የተነገረው ትንቢቱን ለሚናገረው ነቢይ አንድን ጥቅም ወይም ክብር ለማስገኘት ታስቦ ከሆነ፥ እንዲህ ዓይነቱን መልእክት ስንቀበል ልንጠነቀቅ ይገባል።

<u>አራተኛ</u>፥ ትንቢቱን የሚናገረውን ግለሰብ ምን ያህል እናውቀዋለን? የሚለው ጥያቄ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሆኑ ምእመናን የሚያውቁት ሰው ብድግ ብሎ ትንቢትን በሚናገርበት ጊዜ ይህንኑ ትንቢት በአጥጋቢ ሁኔታ መመርመሩ አስቸጋሪ ነው። አንድ አዲስ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ትንቢት ለመናገር በሚፈልግበት ጊዜ መሪዎቿ መጀመሪያ ሊሰሙትና መልእክቱን ሊገመግሙት ይገባል። እግዚአብሔር መሪዎች ቤተ ክርስቲያናቸውን ከስሕተት እንዲጠብቁ ኃላፊነት ሰጥቷቸዋል። ብዙውን ጊዜ የሐሰት ትምህርቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡት ትንቢትን ወይም ትምህርትን በሚሰጡ ያልታወቁ ሰዎች አማካኝነት ነው። ግለሰቡ ትንቢቱን

ወይም ትምህርቱን ለሕዝቡ ሁሉ ማስተላለፍ ያለበት መሪዎቹ መልእክቱን ከገመገሙት በኋላ መሆን አለበት። ልብ አድርግ የሐሰት ትምህርት አንድ ጊዜ ወደ ሕዝቡ ዘልቆ ከገባ በኋላ በስፋት እንዳይሰራጭ መከላከሉ ከባድ መሆኑን አትዘንጋ። ነገር ግን እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ከቃሉ ጋር የሚስማማ መልእክት ለማስተላለፍ የሚጠቀምበትን አገልጋይ ካወቀ፥ አናናራቸው የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚከተል እንገነዘባለን። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ለምእመናን የእግዚአብሔርን ቃል በይፋ እንዲናገር ልንፈቅድለት እንችላለን።

አምስተኛ፥ የተነገረው ትንቢት ወደፊት የሚፈጸም ከሆነና በተነገረበት መንገድ በትክክል ካልተፈጸመ፥ ይህ ትንቢት ከእግዚአብሔር እንዳልመጣ ልናረጋግጥ እንችላለን። ከዚህ በኋላ ይህን ትንቢት የተናገረውን ግለሰብ ልንጠራጠር እንችላለን።

18ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያን፥ በተለይም ወጣቶች መሪዎቻቸውን ለማክበር የሚፈልጉት በምን መንገድ ነው። ይህንን በበለጠ እንዲያከናውኑት ምን ትመክራቸዋለህ? ለ) ጳውሎስ በዚህ ስፍራ እንደገለጸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኃላፊነታቸውን በአጥጋቢ ሁኔታ ለመወጣት ምን ሊያደርጉ ይገባል? ሐ) ኣንድ ትንቢት በትክክል ካለመፈተኑ የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተለያዩ ችግሮችን ስላስከተለበት ሁኔታ ምሳሌዎችን ስጥ። መ) ትንቢት ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ እድገትን ስላመጣበት ሁኔታ ግለጽ። ሠ) መልካም የሆነው አሳብ ለሕዝብ እንዲቀርብና ሐሰተኛ የሆነው መልእክት እንዳይሰራጭ ለመከላከል ቤተ ክርስቲያን ልትጠቀም የምትችላቸው ዘዴዎች ምን ምንድን ናቸው?

4. ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች በሁለንተናቸው፥ ማለትም በሥጋቸው፥ በነፍሳቸውና በመንፈሳቸው በቅድስና እንዲያድጉ ይጸልያል። ይህም ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ እንከን የሌላቸው እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። ጳውሎስ እግዚአብሔር በእነዚህ አዳዲስ አማኞች ሕይወት ውስጥ በመሥራት እንደሚያሳድጋቸው እርግጠኛ ነበር።

ጳውሎስ እነዚህ አዳዲስ ክርስቲያኖች በጸሎት እንዲተጉ በመጠየቅ መልእክቱን ይደመድማል። እርስ በርሳቸውም ያላቸውን ፍቅር በተቀደሰ አሳሳም እንዲገልጹ ያሳስባቸዋል። በመሳሳም ሰላምታ መለዋወጡ በመደበኛነት የሚገለጽ ሥርዓታዊ ተግባር ሳይሆን፥ አማኞች እርስ በርሳቸው ያላቸውን ፍቅርና መስጠት የሚገልጹበት ሊሆን ይገባል። ጳውሎስ ይህ መልእክት ለክርስቲያኖች ሁሉ እንዲነበብ ካሳሰበ በኋላ ቡራኬ በመስጠት መልእክቱን ይደመድማል።

19ኛ ጥያቄ፡- ከ1ኛ ተሰሎንቄ ውስጥ ሕይወትህን የባረኩ አንዳንድ ነጥቦች ምንድን ናቸው?

## ሦስተኛ ቀን 2ኛ ተሰሎንቄ

እንግዳ ወርቅ ተወልዶ ያደገው በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር። ቤተሰቦቹ ትምህርት ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘባቸው ብዙ ጥረት አድርገው ትምህርት ቤት አስገቡት። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ካጠናቀቀ በኋላ ሥራ መፈለግ ጀመረ። ያገኘው ሥራ ግን አነስተኛና ዝቅተኛ ክፍያ የሚከፈልበት

ነበር። እርሱ ግን ይህ ለክብሬ የሚመጥን ሥራ አይደለም ብሎ በማሰቡ ቀኑን ሙሉ ሲንቀዋለል ቆሞ ይውል ጀመር። የግብርና ሥራ ለማከናወንም የትምህርት ደረጃው እንደማይፈቅለት አሰበ። ወላጆቹን ለመጎብኘት ወደ አገር ቤት በተመለሰ ጊዜ በእርሻ፥ በአረምና በእንጨት ፈለጣ ዘመዶቹን ለመርዳት አልፈለገም። ነገር ግን ወላጆቹ የሚያስፈልጉትን ነገሮች እንዲያሟሉለት ጠበቀ። ቀኑን ሙሉ ከጓደኞቹ ጋር ሲነጋገርና ከቤት ወደ ቤት እየዞረ ቡና ሲጠጣ ይውላል። እንግዳ ወርቅ ምንም ሥራ ስላልነበረው ብዙ ትርፍ ሰዓታት ነበሩት። በዚህም ጊዜ ውስጥ መጥፎ ልማዶችን ያስተናግድ ጀመር። ሥራ ከመፈለግ ይልቅ በሱቆች አካባቢ መዋልን መረጠ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጓደኞቹ ጫት መቃም አስለመዱት። ብዙም ሳይቆይ ወደ መጠጥ ቤቶችና ሴተኛ አዳሪዎች ዘንድ ጎራ ማለት ጀመረ። በመጨረሻም በኤድስ በሽታ ተይዞ ሞተ።

20ኛ ጥያቄ፡- ሀ. እንግዳ ወርቅ ለአነስተኛ ሥራዎች የነበረው አመለካከት ምን ዓይነት ነበር? ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ይመስልሃል? ለ) ሥራ በፈታ ጊዜ ምን ዓይነት አሳቦች ወደ አእምሮው መጡ? ሐ) ሥራ መፍታቱ ምን ዓይነት ውጤት አስከተለ?

ሐዋርያው ጳውሎስ ማንኛውም ሥራ ክቡር መሆኑን አስተምሯል። አንዳንድ ሥራ ለተማሩት ሰዎች የማይገባና ትናንሽ ሥራዎችን ከመሥራት ይልቅ ዝም ብሎ መቀመጡ ተገቢ እንደሆነ የሚያስተምረው ዲያብሎስ ነው። አንዳንድ የተሰሎንቄ አማኞች ሥራ አቁመው የክርስቶስን መምጣት በሚጠባበቁበት ጊዜ ጳውሎስ እያንዳንዱ ክርስቲያን እንዲሠራ አዟል። ጳውሎስ ታላቅ ሐዋርያ የሆነው ራሱ ሳይቀር የሌሎች ሸክም እንዳይሆን ቀንና ሌት ይሠራ እንደነበር ገልጾአል (2ኛ ተሰ. 3፡8)። ጳውሎስ ለዚህ ጉዳይ ትልቅ ትኩረት በመስጠቱ አንድ ሰው ለመሥራት ካልፈለገ መብላት እንደሌለበት አስረድቷል። ጳውሎስ በተጨማሪም እነዚህ ሊሠሩ የማይፈልጉ ክርስቲያኖች እንደ ዓለማውያን የሚቆጠሩ መሆናቸውን ገልጾአል። ሌሎች አማኞች ከእነዚህ ሥራ ከማይወዱ ሰዎች ጋር ኅብረት መፍጠር አያስፈልጋቸውም ነበር (2ኛ ተሰ. 3፡9-15)። ብዙም ለተማሩት ሰዎች የሚስማማ ሥራ በማይበዛበት በዚህ ዘመን ክርስቲያን ወጣቶች መሥራትን አቁመው በወላጆቻቸው ላይ ሊደገፉ ይችላሉ። ይህ ግን ለወንጌሉ እንቅፋት ነው። አነስተኛ ሥራዎችን መፈለግ ወይም ወደ ግብርና ተመልሶ ማረሱ በጣም ጠቃሚ ነው። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሥራቸውን በማክበር በጊዜው ሊያነሣቸውና የተሻለ ሥራ ሊሰጣቸው ይችላል።

21ኛ ጥያቄ፡- 2ኛ ተሰ. 1-3 አንብብ። ሀ) ጳውሎስ ለክርስቶስ እንደሚገባ ስለመኖር ምን ይላል? ለ) ጳውሎስ ስለ መጨረሻው ዘመን የሚያስተምረውን አብራራ።

**ጳውሎስ የኋላ ኋላ አሳዳጆቻቸው ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ለፍርድ እንደሚጋለጡ በማሳሰብ በስደት ላይ ያሉትን አማኞች ያበረታታቸዋል (2ኛ ተሰ. 1)።**

ብዙውን ጊዜ ለክርስቲያኖች ስደትን በደስታ ተቀብሎ ማስተናገዱ ቀላል አይደለም። በመሆኑም እግዚአብሔር ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ላይ ከሆነ

እነዚህ ክፉ ሰዎች እንዲያሳድዱን የሚፈቅደው ለምንድን ነው ብለን እንጠይቃለን። ወይም እግዚአብሔር አፍቃሪ አምላክ ከሆነ እንዲህ ዓይነቱ ስደት እንዲደርስብን ለምን ይፈቅዳል? ለብዙ ክርስቲያኖች በተለይም ብዙ ስደት ላልደረሰባቸው የክርስቲያኖች ልጆች እግዚአብሔር ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች ሁሉ ይጠብቀናል ብሎ ማመኑ ቀላል ነው። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየትኛውም ስፍራ እንዲህ ዓይነት የተስፋ ቃል አልተገባልንም። ይልቁንም በሁሉም የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ማለት ይቻላል፥ እንደ እግዚአብሔር ልጆች ስደትንና መከራን እንደምንቀበል ተገልጾአል። ስለሆነም አስፈላጊው ነገር ከስደት ለመሸሽ መሞከሩ ሳይሆን በስደት ውስጥ ተገቢውን ባሕርይ መጎናጸፋችን ነው።

የተሰሎንቄ አማኞች ገና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሳይጠነክሩ ለስደት ተጋልጠው ነበር። በክርስቶስ ካመኑበት ጊዜ ጀምሮ በአይሁዶች ወይም በአሕዛብ ሲሰደዱ ቆይተዋል። ጳውሎስ በስደቱ የደረሰባቸውን ተስፋ መቁረጥ ስለ ሰማ ሰላምታ ካቀረበላቸው በኋላ ስደትን የሚመለከት ትምህርት ያቀርብላቸዋል።

1. ጳውሎስ አማኞቹን ለእድገታቸው ያበረታታቸዋል። በእምነት፥ እርስ በርሳቸው ላላቸው ፍቅርና በስደት ውስጥ እምነታቸውን ይዘው ለማቆየት በመቻላቸው ያመሰግናቸዋል። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ በአመዛኙ ሁሉም ነገር መጥፎ ይሆናል ብለን እናስባለን። ነገር ግን ጳውሎስ እግዚአብሔር የመከራ ጊዜያትን በመጠቀም እንዴት መንፈሳዊ ሕይወታችንን እንዳሳደገው እንድናስታውስ ይፈልጋል።

2. ጳውሎስ በመከራ ውስጥ ያሉት ክርስቲያኖች ወደፊት እንዲመለከቱና የመጨረሻውን ዘመን እንዲያስታውሱ በማድረግ ያበረታታቸዋል። ለአማኞች በስደት መጽናቱ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በሚገቡበት ጊዜ ልማትና ክብርን ያስገኝላቸዋል። ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ *መከራን ለተቀበሉት አማኞች እፎይታን ያጎናጽፋቸዋል።* ራእይ 21:4 እንደሚያስረዳው በእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ውስጥ እንባዎች አይኖሩም። መከራም ሆነ ሞት በዚያ ስፍራ የላቸውም። ይህንኑ መጪ የእግዚአብሔር መንግሥት ካስታወስን አሁን የምንጋፈጠውን ጊዜያዊ ፈተና ልንታገሥ እንችላለን (2ኛ ቆሮ. 4:16-18 አንብብ)።

በአንጻሩ በመጨረሻው ዘመን የሚያምኑ ሰዎችና ስደትን ለማምጣት ሰይጣን በመሣሪያነት የተጠቀመባቸው ሰዎች ለከፍተኛ ቅጣት ይጋለጣሉ። እግዚአብሔር ጻድቅ ስለሆነ ለሰዎች የሥራቸውን ይከፍላቸዋል። አማኞች የዘላለምን ሕይወት ሲያገኙ የማያምኑ ሰዎች ግን የዘላለም ጥፋት ይጠብቃቸዋል። እግዚአብሔር ካለበት ስፍራና ከግርማው ኃይል ይርቃሉ። ሲኦል የቅጣት ሥቃይ የሚታይበት ብቻ አይደለም። ይህ ሰዎች ለዘላለም ከእግዚአብሔርና ከእግዚአብሔር በረከቶች የሚለዩበት ነው። በምድር ላይ የማያምኑ ሰዎች ከእግዚአብሔር በረከቶች አንዳንዶችን ያገኛሉ። ከእነዚህም መካከል ጤና፥ ምግብ፥ ዝናብና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል። በሲኦል ግን ከእነዚህ በረከቶች አንዳቸውንም ሊያገኙ አይችሉም።

3. ጳውሎስ አማኞች *ለእግዚአብሔር ጥሪ እንደሚገባ ይኖሩ ዘንድ* የሚጸልይላቸው መሆኑን ይናገራል። እግዚአብሔር በሕይወታቸው ውስጥ ስደትንም ጨምሮ በኃይል እንዲሠራና ለእነርሱ የወጠናቸውን ዕቅዶች ሁሉ የሚፈጽሙበትን ኃይል እንዲሰጣቸው ይጸልያል።

22ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በሕይወትህ የደረሱብህን አንዳንድ መከራዎች ዘርዝር። በእነዚያ አስቸጋሪ ጊዜያት ውስጥ ሳይቀር እግዚአብሔር ታማኝነቱን የገለጸልህ እንዴት ነው? በሕይወትህ ውስጥ ምን ለውጦች ተከሰቱ? ችግሮች በሚያጋጥሙን ጊዜ እነዚህኑ በረከቶችና እድገት ማስታወሱ ለምን ይጠቅማል? ለ) ለክርስቲያኖች ከምድራዊ ሥቃይና ስደት ይልቅ በሰማያዊ የዘላለም በረከቶች ላይ አጽንኦት መስጠቱ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? የወደፊት በረከቶችን በምንዘነጋበት ጊዜ ምን ይከሰታል? ከአሁኑ ቀላል ሕይወት ይልቅ ዓይኖቻችንን በዘላለማዊ መንግሥት ላይ በምንተክልበት ጊዜ ምን ይከሰታል? ሐ) ጳውሎስ ለጥሪያችን እንደሚገባ እንድንኖር ሲናገር ምን ማለቱ ነው? ለመጠራታችን እንደሚገባ የምንኖርባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

## ጳውሎስ ክርስቶስ የዐመፁ ሰው ሳይገለጽ እንደማይመለስና አማኞች በታማኝነት ሊመላለሱ እንደሚገባ ያስተምራል (2ኛ ተሰ. 2)።

እንደዛሬው ዘመን ሁሉ በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ መጨረሻው ዘመን ከፍተኛ ግራ የመጋባት ሁኔታ ነበር። ጳውሎስ የሁለተኛ ተሰሎንቄን መልእክት የጻፈበት ዋናው ምክንያት ይህንኑ ግራ መጋባት ለማስተካከል ነበር። በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ መጨረሻው ዘመን እርስ በርሳቸው የሚጋጩና በአማኞች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን የሚያስከትሉ ሁለት ዓይነት ትምህርቶች የነበሩ ይመስላል። በመጀመሪያ፥ ክርስቶስ በቶሎ ይመጣል ብለው የሚያስቡ ወገኖች ነበሩ። ከዚህም የተነሣ ክርስቲያኖች ሥራ አቁመው ነበር። ሁለተኛ፥ ሌሎች ደግሞ የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በጣም እንደ ረፈደባቸው ያስተምሩ ነበር። ክርስቶስ ድሮውኑ ዳግም ተመልሶ እንደመጣና እነርሱ ግን ሊያገኙት እንዳልቻሉ ይናገሩ ነበር። እንዲያውም ከጳውሎስ እንደተጻፈ ተደርጎ የቀረበ ክርስቶስ አስቀድሞ መምጣቱን የሚገልጽ ደብዳቤ ደርሷቸው ነበር። እነዚህን ሁሉ ውዝግቦች ለማርገብ ጳውሎስ ስለ መጨረሻው ዘመን ጠቃሚ ትምህርቶችን ይሰጣል። ጳውሎስ ይህንኑ ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ በመጨረሻው ዘመን በሚከሰቱት መልእክቶች ላይ ያተኩራል። በዚህም ክርስቶስ ከዚህ በፊት ዳግም እንዳልተመለሰ ያብራራል። ከእነዚህም ምልክቶች አንዳንዶቹ ምን ምን ነበሩ?

ሀ) ጳውሎስ በመጨረሻው ዘመን ዐመፅ እንደሚበዛ ያስረዳል። እንደውም ጳውሎስ ይህንኑ ዘመን ዐመፅ ይለዋል። ይህም በዓለም ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በእግዚአብሔር ላይ ከፍተኛ ዐመፅ የሚቀሰቀስበት ዘመን መሆኑን ለማስረዳት ነው።

ለ) ይህ የዐመፅ ጊዜ፥ የዐመፅ ሰው ወይም *የጥፋት ሰው* ተብሎ በሚታወቀው ግለሰብ ይመራል። ይህ ሰው ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት መገለጥ ይኖርበታል። ጳውሎስ የዚህን ሰው ክፉ ባሕርያት በሦስት መንገዶች

ያብራራል። በመጀመሪያ፥ በሥርዓት የለሽነት የተሞላ መሆኑን ያስረዳል። ይህ የዐመፅ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግጋት ለማፈራረስ የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር ቀድሞውኑ ፍጻሜውን ወስኗል። ይህ ሰው ለአጭር ጊዜ በዓለም ሁሉ ላይ ሥልጣን ሊኖረው ቢችልም፥ እግዚአብሔር ግን በመጨረሻው ያሸንፈውና ወደ ሲኦል ይሰድደዋል (ራእ. 19፡19–20 አንብብ)። ሦስተኛ፥ ይህ ዐመፀኛ ራሱን እንደ አምላክ በመቁጠር ሰዎች እንዲያመልኩት ያስገድዳቸዋል። እግዚአብሔርንም እንዲቃወሙት ያነሣሣቸዋል።

ምሁራን ይህ የዐመፅ ሰው ማን ይሆን በሚለው ጉዳይ ላይ እርስ በርሳቸው ይከራከራሉ። አንዳንዶች ጳውሎስ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት የሚታየውን የመጨረሻው ዘመን አስከፊ ሁኔታ በተምሳሌት እየተናገረ ነው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ጳውሎስ እንደ ኔሮ ወይም ዶሚቲያን ስላሉት ክፉ የሮም መሪዎች እየተናገረ ነው ይላሉ። እነዚህ ሰዎች ጳውሎስ መልእክቱን ከጻፈ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ በቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ያስከትሉ ነበር። ነገር ግን ጳውሎስ ስለ ሐሳዊ መሢሕ የሚናገር ይመስላል። ይህም በራእይ መጽሐፍ ውስጥ አውሬው የተባለው የመጨረሻው የዓለም ገዢ ነው (ራእ. 13)።

ጳውሎስ የዐመፀኝነት ምሥጢራዊ ኃይል ሁልጊዜም ይሠራ እንደነበር ይናገራል። ከእግዚአብሔር ጋር በመጣላት ሕዝቡን የሚያሳድዱ መሪዎች ሁልጊዜም ሲታዩ ኖረዋል። በመጨረሻው ዘመን ግን ልዩ የዐመፅ የታላቅ ክፋትና የስደት ጊዜ ይመጣል። ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች ክርስቶስ ሳናውቀው መጥቶ ተመልሷል ብለው እንዳይሠጉ ያሳስባቸዋል። ምክንያቱም ይህ ታላቅ የክፋት ጊዜ ገና አልደረሰምና። የተሰሎንቄ አማኞች ክርስቶስ መቼ እንደሚመጣ ወይም ደግሞ ቀድሞውኑ መጥቶ እንደሆነ እንዴት ልናውቅ እንችላለን ሲሉ ጳውሎስን ጠይቀውታል። ጳውሎስ በዓለም ሁሉ ላይ የሚገዛው ክፉ መሪ አለመገለጹ ክርስቶስ ዳግም እንደ ተመለሰ የሚያውቁበት አንደኛው መንገድ እንደሆነ ያስረዳል።

ሐ) ዐመፃን የሚከለክለው ገና አልተወሰደም። ነገር ግን ይህ ዐመፅን የሚከለክለው ማን ነው? አንዳንድ ምሁራን ይህ ዐመፅን የሚከለክለው እግዚአብሔር የሚቆጣጠረው የሰዎች መንግሥት እንደሆነ ያስባሉ። የሮም መንግሥት በጳውሎስ ዘመን የክፋትን ስርጭት ይቆጣጠር ነበር። የእኛም መንግሥታት በዘመናችን ውስጥ ያሉትን የክፋት ሥራዎች ይቆጣጠራሉ። በመጨረሻው ዘመን ግን ይህ የዐመፅ ሰው መንግሥታትን ሁሉ ስለሚቆጣጠር ማንም ክፋትን የመፈጸም ዓለም አቀፋዊ ኃይሉን ሊቀንስበት አይችልም። ይሁንና ጳውሎስ የሚናገረው ስለ መንፈስ ቅዱስ ይመስላል። እግዚአብሔር ለመንፈስ ቅዱስ በዓለም ውስጥ የሚሰራጨውን የክፋት ኃይል ለመቀነስ አገልግሎት የሰጠው ይመስላል። ስለሆነም ሐሳዊ መሢሕ ሥልጣን ከመያዙ በፊት የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ከዚህ ዓለም ይወሰዳል። ሌሎች ደግሞ ይህንኑ ሁኔታ ከአማኞች መነጠቅ ጋር በማዛመድ ዛሬ በአማኞች ልብ ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ጋር እንደሚወሰድ ይናገራሉ። በዚያ የዐመፃ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የሚሠራው ልክ በብሉይ ኪዳን ዘመን ይሠራ

እንደነበረው ይሆናል። ሁሉንም የእግዚአብሔር ልጆች ከመሙላት ይልቅ በአንዳንድ ሰዎች ላይ ብቻ ይመጣል።

መ) ክርስቶስ በአፉ እስትንፋስ ሐሳዊ መሢሕን በማሸነፍ ኃይሉን ያስወግዳል። (ክርስቶስ ይህን የሚያደርገው በቃሉ ትእዛዝ ይሆናል)። ክርስቶስ ይህን የመጨረሻውን ክፉ የዓለም መሪ በመገለጡ ኃይል በቀላሉ ያሸንፈዋል።

ሠ) ሐሣዊው መሢሕ የሰይጣንን ኃይል በመላበስ ሁሉንም ዓይነት ተአምራት ይፈጽማል። በዚህም አምላክ መሆኑንና ሰዎች ሊያመልኩት እንደሚገባ ያሳምናቸዋል።

ረ) በመጨረሻው ዘመን ወንጌሉን ሊሰሙ ያልፈቀዱ ሰዎች የሐሳዊው መሢሕን ውሸት ያምናሉ። በመሆኑም ከሐሳዊው መሢሕ ጋር አብረው ይጠፋሉ።

በዚህ የዓመፅ ዘመን ክርስቲያኖች በምድር ላይ ይኖሩ ይሆን? ትላንት እንደ ተመለከትነው፥ ክርስቲያኖች ይህንን የክፋት ዘመን እንደሚጋፈጡና ለክርስቶስ በታማኝነት ጸንተው ሊያልፉ እንደሚገባ የሚናገሩ አያሌ ምሁራን አሉ። ነገር ግን መጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን እንደምትነጠቅና በአፋቸው ክርስቲያኖች ነን የሚሉት ብቻ ከዐመፅ ሰው ጋር እንደሚጋፈጡ ያስተምራሉ። እነዚህ የአፍ ክርስቲያኖች ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ሳይነጠቁ የቀሩ ናቸው። ትክክለኛው አመለካከት እንግዲህ የትኛው ነው? ይህን ሁኔታ መወሰኑ አስቸጋሪ ነው። ምንም እንኳን በራእይ 6–19 እንደተገለጸው ይህንን በዚህ የዐመፅ ጊዜ ውስጥ ባንገባ ደስ ቢለንም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ጉዳዩን በግልጽ አያብራራም። ስለሆነም አማኞች በዚህ የመከራ ጊዜ ውስጥ ሊያልፉ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን ተስፋችንና ትኩረታችን በዚህ የክፋት ዘመን ውስጥ አለመግባት ሳይሆን፥ ለክርስቶስ ታማኝ ሆኖ መጽናት ሊሆን ይገባል። በዚህ ጊዜ ክርስቶስ ከመከራ በፊት ቢወስደን ወይም ደግሞ በዚህ የክፋት ዘመን ውስጥ ቢያሳልፈን፥ ክርስቶስን በማስከበር በዘላለሙ መንግሥት በእርሱ እንሸለማለን።

ጳውሎስ ይህንን ክፍል የሚያጠናቅቀው የተሰሎንቄ አማኞች የክርስቶስን ምጽአት በሚጠባበቁበት ጊዜ እንዴት ሊመላለሱ እንደሚገባ በመምከር ነው። እግዚአብሔር እንደመረጣቸውና ሊቀድሳቸው በውስጣቸው እየሠራ መሆኑን በመገንዘብ ልበ ሙሉነት ሊሰማቸው ይገባ ነበር። እንዲሁም ከጳውሎስ የሰሙትን የወንጌል እውነት ጠብቀው በታማኝነት ሊኖሩ እንደሚገባ ያስረዳል።

---

23ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ይህ ስለ መጨረሻው ዘመን የሚናገረው ትምህርት ክርስቶስ በዚህ ቀን ይመጣል ለሚሉ ሰዎች መልስ እንድንሰጥ የሚረዳን እንዴት ነው? ለ) ክርስቶስ የሚመጣበት ቀን ከመገመት ይልቅ እርሱ በሚመለስበት ጊዜ እንዳናፍር በሕይወታችን ምን ልናደርግ ይገባል?

---

## ጳውሎስ አማኞች የክርስቶስን ምጽአት በሚጠባበቁበት ጊዜ ትጉሕ ሠራተኞች ሆነው ሊመላለሱ እንደሚገባ ያስተምራል (2ኛ ተሰ. 3)

ጳውሎስ ይህን አጭር የሁለተኛ ተሰሎንቄ መልእክት የሚያጠቃልለው የተሰሎንቄ አማኞች አንዳንድ ነገሮችን እንዲፈጽሙ በመጠየቅ ነው። እነዚህም ነገሮች ክርስቲያኖች የክርስቶስን ምጽአት በሚጠባበቁበት ጊዜ ስሙን በሚያስከብር መንገድ እንዲኖሩ የሚያግዙአቸው ናቸው።

1) አማኞች ጳውሎስ ወንጌልን በስፋት እንዲያሰራጭ በጸሎት ሊደግፉት ይገባ ነበር። ክፉ ሰዎች በተለይም የሐሰት አስተማሪዎች የወንጌሉን ዘር እንዳያጠፉ መጸለይ ይገባቸው ነበር። ጳውሎስ እግዚአብሔር የተሰሎንቄን አማኞች ከእነዚህ ክፉ ሰዎችና ከሐሰተኛ ትምህርታቸው እንደሚጠብቃቸው እርግጠኛ መሆኑን ይናገራል። እኛም በአገራችንና በዓለም ሁሉ ወንጌሉ በስፋት እንዲሰራጭ በዋናነት ልንጸልይ ይገባል።

2) ጳውሎስ ክርስቲያኖች ሥራ በመፍታታቸው በጽኑ እያስጠነቀቀ ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ያሳስባቸዋል። የተሰሎንቄ አማኞች የእርሱን ምሳሌነት በመከተል ተግተው እንዲሠሩ ይመክራቸዋል። ቤተ ክርስቲያን ሊሠሩ በማይፈቅዱት ሰዎች ላይ ቅጣት እንድትጥልና ማንኛውም አማኝ ከእነርሱ ጋር ኅብረት እንዳያደርግ አዟል። ክርስቶስ መቼ እንደሚመለስ በትክክል ስለማናውቅ ተግተን እየሠራን፥ ስለ ወደፊቱ እያቀድን፥ ልጆቻችንን እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እያሳደግን፥ ወዘተ... ጤናማ ሕይወት መኖራችንን መቀጠል ይኖርብናል። እንዲሁም እግዚአብሔርን የሚያስከብር የተቀደሰ ሕይወት መኖር ይገባናል። በዚህ ዓይነት የምንመላለስ ከሆነ ክርስቶስ ዛሬ፥ ነገ፥ ከአምስት ዓመታት በኋላ ወይም ከአንድ ሺህ ዓመታት በኋላ ቢመለስ፥ እርሱን በሚያስከብር መንገድ ባለመኖራችን ለኃፍረት አንጋለጥም።

ጳውሎስ ከስደትና የሐሰት ትምህርት ጫና ባሻገር ልባቸውን የሚሞላ የእግዚአብሔር ሰላም እንዲኖራቸው በመመኘት ይህንን መልእክት ያጠናቅቃል። ከዚያም በመልእክቱ ላይ የእርሱ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስሙን ይጽፋል።

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፡- ከ2ኛ ተሰሎንቄ መጽሐፍ ጠቃሚ ትምህርቶችን ዘርዝር። |

## አራተኛ ቀን፣ ለሳምንታዊ ስብሰባ በመዘጋጀት የዚህን ክፍል ትምህርት ከልስ።

# ሳምንታዊ ስብሰባ

## የመወያያ ጥያቄዎች፡-

1. ሀ) ጳውሎስ በ1ኛና በ2ኛ ተሰሎንቄ ውስጥ ስለ መጨረሻው ዘመንና የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ያስተማራቸው ጠቃሚ እውነቶች ምን ምንድን ናቸው? ለ) ክርስቶስ ቀደም ሲል እንደ ተመለሰ ወይም በዚህ ቀን ይመለሳል የሚሉ ትምህርቶች አጋጥመውሃል። ከሆነ ይህ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያስከተለው ውዝግብ ምን ነበር። ሐ) ይህ በሰዎች አኗኗር ላይ ያስከተለው ተጽዕኖ ምን ነበር? መ) ቤተ ክርስቲያን በማያምኑ ሰዎች ላይ በነበራት ምስክርነት ላይ ምን ተጽዕኖ አስከተለ? ሠ) ሰዎች ሁሉ ክርስቶስ በዚህ ሳምንት ይመለሳል በሚል ተስፋ ቢመላለሱ አኗኗራቸው እንዴት ይለወጣል?

ረ) ክርስቶስ የሚመለሰው ረጅም ጊዜ ወይም ደግሞ በሚቀጥለው ሳምንት መሆኑ የቤተ ክርስቲያናችንን አኗኗርና ዕቅድ የሚለውጠው እንዴት ነው?

2. ሀ) ጳውሎስ የሞቱ አማኞች ምን ይሆናሉ ብሎ አስተማረ? ለ) አዲስ ኪዳን ሳያምኑ የሚሞቱ ሰዎች ምን ይሆናሉ አለ? ሐ) አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ (ልክ ክርስቶስ በዮሐ. 11፡35 እንዳደረገው) በማልቀስና ዛሬ ብዙ ሰዎች እንደሚያደርጉት በተስፋ ቢስነት በመጮህ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? መ) ክርስቲያኖች በትንሣኤ ሙታን ላይ ያላቸውን እምነት ጸንተው ቢኖሩት በሞት፥ በስደትና በተቀደሰ አኗኗር ላይ የሚኖራቸው አመለካከት እንዴት ይለወጣል?

3. ሀ) ጳውሎስ በ1ኛ ተሰ. 1፡3 የተሰሎንቄን አማኞች እንዴት ይገልጻቸዋል? ለ) እነዚህ ሦስት ባሕርያት ለእያንዳንዱ ክርስቲያን እንዴት እንደሚያስፈልጉ አብራራ። ሐ) የአንድ አማኝ ሕይወት የእነዚህን ሦስት ባሕርያት መኖር እንዴት ሊያሳይ እንደሚችል ምሳሌዎችን ስጥ። መ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በዚህ መንገድ የሚገለጹ ይመስልሃል? ካልሆነ ለምን? ሠ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አባሎቻቸው እንደ ተሰሎንቄ አማኞች ይሆኑ ዘንድ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

4. ሀ) ጳውሎስ በ1ኛና በ2ኛ ተሰሎንቄ፥ አማኞች ከሥራ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የገለጸው እንዴት ነው? ለ) ብዙ ወጣቶች ዝቅተኛ ነው ብለው የሚያስቡትን ሥራ ለመሥራት የማይፈልጉት ለምንድን ነው? ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ይመስልሃል? ሐ) በሥራ ላይ በማንሆንበት ጊዜ የሚመጡብን ተጨማሪ ፈተናዎች ምንድን ናቸው? መ) ጳውሎስ በሥራ ላይ ያልተሰማሩትን ሰዎች በጽኑ የሚገሥጸውና የወሲብን ኃጢአት እንደፈጸሙ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ቅጣት ሊደርስባቸው እንደሚገባ የሚናገረው ለምንድን ነው?

5. ሀ) ስለ መጨረሻው ዘመን የሚናገሩ አራት ዐበይት አመለካከቶች ምን ምንድን ናቸው? ለ) ከእነዚህ አመለካከቶች የትኛውን ታምናለህ? ሐ) ቤተ ክርስቲያንህስ? መ) ክርስቶስ በዚህ ቀን ይመጣል ከማለት ይልቅ አንድ ቀን እንደሚመለስ፥ ሙታንን እንደሚያስነሣ፥ በሕይወት ያሉትን እንደሚለውጥና ለዘላለሙም ከእርሱ ጋር አብረን እንደምንኖር ማመኑ የበለጠ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሠ) ክርስቲያኖች ያልሆኑ ሰዎችና ሥጋዊ ክርስቲያኖች የሚፈጽሙአቸውና ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ የሚያፍሩባቸውን ነጥቦች ዘርዝር። ረ) ክርስቲያኖች ክርስቶስ በየትኛው ጊዜ ሊመጣ እንደሚችል በሚያሳይ መልኩ ሊመላለሱ የሚችሉባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ሰ) ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን በሚያስደስት መልኩ የማይኖሩት ለምንድን ነው? እነዚህ ሰዎች ስለ ክርስቶስ መመለስ የዘነጉት ነገር ምንድን ነው?

6. ሀ) ትንቢትን ለመመርመር የምንጠቀምባቸው አምስት ፈተናዎች ምን ምንድን ናቸው? አንተ የምታስባቸው ሌሎችም ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው መመዘኛዎች አሉን? ለ) የትንቢት ቃል ቤተ ክርስቲያንን በዕውቀትና እግዚአብሔርን በመምሰል እንድታድግ ያበረከተው አስተዋጽኦ

ምንድን ነው? ሐ) እነዚህን አምስት መመዘኛዎች ካለመጠቀማቸው የተነሣ በቤተ ክርስቲያንህ ወይም በሌላ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተከሰቱትን ችግሮች ግለጽ? መ) የተሳሳቱ ትምህርቶችን ለማስወገድ ቤተ ክርስቲያንህ ምን ዓይነት የትንቢት መፈተኛ ዘዴዎችን ልትጠቀም ይገባል?